# ምዕራፍ 17

## የወንጌሎች መልእክት

በዚህ ምዕራፍ ውስጥ በወንጌላት ውስጥ የሚገኙትን ዋና ዋና ነጥቦች እናጠናለን። ይህን ስናደርግ እነዚህ ወንጌሎች ምንም ግንኙነት የሌላቸው ታሪኮች ሳይሆኑ በሚገባ የተቀናጁና በአንድ ዓላማ የተሣሡሩ መሆናቸውን እንረዳለን።

የመጀመሪያው ዓይነት ጽሑፍ ተአምራት ነው። ወንጌላቱ በሙሉ ኢየሱስ በፈለገበት ጊዜ ሁሉ ተአምራት በመሥራቱ ይስማማሉ። ምን ጊዜም ተአምራት የእግዚአብሔርን ዓላማና ዕቅድ የሚያሳይ መንገድ ነበር። ተአምራት የሰውን ስሜት ለመሳብ ወይም ሰዎችን ለመርዳት ብቻ አይፈጸሙም። የክርስትና መሠረት ስለሆነ ከተአምራት ሁሉ በላይ የሆነው ተአምር ትንሣኤ ነው። ተአምራት በወንጌላት ሁሉ ውስጥ መገኘቱ አያስደንቀንም። ተአምራትን በምታጠኑበት ጊዜ ይህንን ጥያቄ ጠይቁ፡- ኢየሱስ አንድን ተአምር ሲያደርግ ምን እያስተማረ ወይም ምን እየገለፀ ነበር?

ሁለተኛው ዓይነት ጽሑፍ ማስተማር ነው። የኢየሱስ ትምህርቶች ሁሉ የተያያዙ ናቸው። በብሉይ ኪዳን ውስጥ የተጻፉት ግጥሞች፥ ታሪኮችና ትንቢቶች ሁሉ ሰዎችን ለመሢሑ መምጣት የሚያዘጋጁ ነበሩ ማለት እንችላለን። የኢየሱስ ትምህርቶች በአንድ መንገድ ወይም በሌላ መንገድ የሚናገሩት ስለ ራሱ መንግሥት ነበር። መንግሥቱን መመሥረት የጀመረው በሐዋርያት ሥራ ምዕራፍ 2 መሆኑን እናውቃለን። ማቴዎስ የኢየሱስን መንግሥት «መንግሥተ ሰማያት» ብሎ ይጠራዋል። እኛም የእርሱን አጠራር በመከተል ቤተ ክርስቲያንን መንግሥተ ሰማያት ብለን ብንጠራው አንድ ዓይነት ባይሆንም የተያያዙ ናቸው። ኢየሱስ

ደንዳናነት ለማሳየት የተጻፉ አይደሉም። በወንጌል እነዚህን የመሳሰሉ ብዙ ታሪኮች ለምን እንደተጻፉ ለመረዳት ሮሜ 9-11 ያለውን ማንበብ ይጠቅማል።

ከአይሁድ ወገን ያመኑት ክርስቲያኖች ካላቸው አስቸጋሪ ጥያቄ አንዱ ብዙዎቹ አይሁዶች ለምን መሢሁን አልተቀበሉትም? የሚል ነበረ። እግዚአብሔር የኢየሱስን ማንነት ግልጽ በሆነ መንገድ ስላልነገራቸው ነውን? ለዚህ ጥያቄ በወንጌሎች ስለ ተቃውሞ የተጻፉት ጽሑፎች መልስ ይሰጡናል። ኢየሱስ በቃልና በተግባር መሢህ መሆኑን ነግሯቸው ነበር፤ ነገር ግን አልተቀበሉትም። እርሱ ብዙ ተከራከራቸው፤ ያልገባቸውንም ነገር እያስተካከለ ገለጸላቸው። እነኝህን የተቃውሞ ታሪኮች በምታነቡበት ጊዜ የሚከተሉትን ሁለት ጥያቄዎች ራሳችሁን ጠይቁ:- ኢየሱስ አይሁዶችን ምን ለማስተማር ሞከረ? አይሁዶች ኢየሱስን እንዳይቀበሉ ችግር የፈጠረባቸው የተሳሳተ አመለካከታቸው ምን ነበር?

አራተኛው ዓይነት ጽሑፍ ኢየሱስ ስለ ራሱ የሚገልጸው ነው። እነኝህ ኢየሱስ በወንጌል ውስጥ ስለ ራሱ የሚገልጽባቸው ምዕራፎች ናቸው። እነኝህን ንግግሮች ብዙዎቹን በዮሐንስ ወንጌል ውስጥ እናገኛቸዋለን። በሌሎቹም ወንጌላት ውስጥ ይገኛሉ። የኢየሱስን ማንነት የሚገልጹ በጣም አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎች እነዚህ ናቸው። አንድ ሰው ስለ ራሱ በሚናገርበት ጊዜ ትክክል ወይም ስህተት ይሆናል እንጂ ሦስተኛ አማራጭ የለውም። ኢየሱስ ስለ ራሱ የተናገረው እውነት ወይም ስሕተት መሆን አለበት። ይህም የተናገራቸውን ሁሉ ያጠቃልላል። ከተናገረው አንዳንዱ ትክክል ነው፤ አንዳንዱ ግን ስሕተት ነው ማለት አንችልም። እነኝህን ምዕራፎች ስታጠኑ እነዚህን ጥያቄዎች ራሳችሁን ጠይቁ:- ኢየሱስ ስለ ራሱ የሚያስተምረው ምንድን ነው? እነዚህ ክፍለ ምንባቦች አዲስ ኪዳን ስለ ኢየሱስ ለሚያቀርበው ትምህርት ሁሉ መሠረት የሚጥሉ ናቸውን?

እንዳለባቸው አበተንራተቸል።

በእነዚህ አምስት ዓይነት ጽሑፎች ላይ ትኩረት ስንሰጥ ጠቅላላውን የወንጌሎች ይዘት ከእነዚህ ሥር ማሰባሰብ አለብን ማለት አይደለም። በዚህ ውስጥ መግባት የማይችሉ ብዙ ምዕራፎች አሉ። እነርሱን ለማስገባት ብለን ልንቀይራቸው አይገባም። ማስታወስ የሚገባን በወንጌል ውስጥ አምስት ዓይነት ጽሑፎች እንዳሉ አስተውለን ማስተማር እንዳለብን ነው። ተማሪዎቻችንንም ደግሞ ይረዳቸዋል።

## ምዕራፍ አሥራ ሰባት - ጥያቄዎች

1. የኢየሱስ ኃይል የተገለጸው እንዴት ነበር?

2. ክርስትና የሚያበሥረው ታላቅ ተአምር የትኛው ነው?

3. የኢየሱስ መልእክት መሠረታዊ ጭብጥ ምንድን ነው?

4. የተቃውሞ ታሪኮች የምንላቸው የሚሰጡን ልዩ ትምህርቶች ምንድን ናቸው?

5. የክርስትና ዋና መሠረት ምንድን ነው?

6. እነዚህን ቃላት ያዘሉት ዘገባዎች ታማኞች ሆነው ካልተገኙ ውጤቱ ምንድን ነው?

7. ኢየሱስ ለተማሪዎቹ የሰጠውን ትምህርት የሚያቀርብልን የትኛው ክፍል ነው?

# ምዕራፍ 18

## በገሊላ የተፈጸሙ ነገሮች

በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ኢየሱስ በገሊላ በነበረ ጊዜ ያደረጋቸውን ነገሮች ጠለቅ ብለን እንመለከታለን። ነገሮቹ የተፈጸሙባቸውን ወቅቶች በአምስት

የተፈጸሙ ነገሮች ልንገነዘብ እንችላለን። በዚህ ወቅት ኢየሱስ ከዚህም በላይ ብዙ ነገሮችን አድርጎ ነበር። ማርቆስ ግን የመዘገበው 17ቱን ብቻ ነው። ማርቆስ 1፡1-39 ከማቴዎስ 3ና 4 እንዲሁም ከሉቃስ 3፡1-5፡11 ጋር ተመሳሳይ ነው። በማርቆስ 3-4 ከተመዘገቡ 17 ነገሮች ውስጥ 16ቱ በሉቃስ ወንጌል ውስጥ ይገኛሉ። ሉቃስ ሳይጠቅሰው ያለፈው ኢየሱስ የመጀመሪያዎቹን አራት ደቀ መዛሙርት መጥራቱን ብቻ ነው (ማቴ.4፡18-22፥ ማር.1፡16-20)።

ማርቆስ 1፡39 አንብቡ። ይህ ጥቅስ በማቴ.5-7 ውስጥ ብቻ ለሚገኘው የተራራው ስብከት መግቢያ ነው። ይህ የገሊላ አገልግሎት ሁለተኛ ክፍል ነው። የማርቆስን ወንጌል በድጋሚ ብንመለከተው፥ ማቴዎስ 5-7 ያለው በማር.ምዕራፍ 1፡39 እና በማር.1፡40 መካከል የሚገባ መሆኑን እንረዳለን። ማር.1፡40-45 ያለው ኢየሱስ በዚያን ወቅት በገሊላ ላደረገው ነገር አጠቃላይ መግለጫ ይሰጠናል። ተመሳሳይ አጠቃላይ መግለጫ በማቴ.5፡1-4ና በሉቃስ 5፡12-16 እናገኛለን። ኢየሱስ በገሊላ ካደረጋቸው ብዙ ነገሮች ውስጥ በዚህ የተጻፉት እነኝሁ ብቻ ናቸው።

ሦስተኛውን ክፍል ደግሞ ትምህርትና ሥልጠና ብለን ልንለየው እንችላለን። በማቴዎስ ወንጌል ብቻ እናገኘዋለን። በማቴ.5-7 የተራራውን ስብከት እናገኛለን። ከዚህ በኋላ አራተኛው ክፍል ወዲያውኑ ይቀጥላል።

አራተኛው ክፍል የተቃውሞ ታሪኮች ብለን ብንጠራው ይረዳናል። በኢየሱስና በአይሁዶች መካከል ስለነበረው ውዝግብ ማቴዎስ አምስት ምዕራፎችን ጽፏል። ከእነኝህ አምስት ምዕራፎች ከተጠቀሱት ነገሮች ውስጥ ማርቆስም ሆነ ሉቃስ የጻፉት ሁለት የተፈጸሙ ነገሮችን ነው። የማቴዎስ መሠረታዊ አቀራረብ ከማርቆስ ጋር ተመሳሳይ ቢሆንም በዚህ

አሁን የማቴዎስ ወንጌል የመጀመሪያዎቹን 7 ምዕራፎች [illegible] ቀላል ነው፤ ምዕ.1-2 የመወለዱ ታሪክ፥ ምዕ.3-4 አገልግሎቱን ሲጀምር፥ ምዕ.5-7 የተራራው ስብከት፥ ምዕ.8-12 ትምህርትና ሥልጠና።

ኢየሱስ በገሊላ ስላደረገው ነገር ዮሐንስም ይነግረናል፤ ሆኖም እርሱ በተለየ ሁኔታ ስላቀረበው በኋላ እንመለከተዋለን። ኢየሱስ አንድን ትምህርት በተለያየ ቦታ ደጋግሞ ስላስተማረ በማቴ.5-7 ያለውና በሉቃስ 6-7 ያለው ትምህርት አንዴ የተሰጠ ነው ማለት አያስፈልግም። በጀመርነው መመሪያ መሠረት በሉቃስ 6-7 የተመዘገቡት ሁኔታዎች ከማቴ.12፡21ና ከማር.3፡6 በኋላ የተፈጸሙ ናቸው። በሉቃስ 6-7 የተመዘገበው ትምህርት የተሰጠው በገሊላ ነው ሆኖም ከማቴ.5-7 ጋር ለየት ባለ ቀን የተሰጠ ነው። ሉቃስ 6-7ን የሚመስል ትምህርት በማርቆስ ወንጌል ውስጥ አይገኝም። ይህ በገሊላ ካቀረበው አገልግሎት አራተኛው ክፍል ነው።

ከገሊላ አገልግሎት አምስተኛውና የመጨረሻው ክፍል አሥራ ሁለቱን ደቀመዛሙርት ማሠልጠን ብለን እንጥራው። ማቴዎስና ዮሐንስ አሥራ ሁለቱ ደቀ መዛሙርት እንዴት እንደተመረጡ አይነግሩንም፤ ይሁን እንጂ ማቴዎስ የ12ቱን ደቀ መዛሙርት ስም ዝርዝር አስፍሯል (ማቴ.10፡2-4)። አመራረጣቸው በትክክል የተገለጸው በማር.3፡13-19ና በሉቃስ 5፡12-16 ውስጥ ነው። ምንም እንኳን ይህ ሁሉ ሲሆን ዮሐንስ ከኢየሱስ ጋር ቢሆንም ስለዚህ ወቅት ምንም ነገር አልገለጸልንም።

ሉቃስ ኢየሱስ በገሊላ ካደረገው ነገር በተለይ በዚህ ነጥብ ላይ የሚሰጠው ዘገባ በጣም አጭር ነው፤ ሉቃስ 8፡1-9፡50 ያለውን ተመልከቱ። ሉቃስ ከምዕ.9 ጀምሮ ኢየሱስ ወደ ኢየሩሳሌም ሲመለስ በመንገድ ያደረገውን ይገልጽልናል።

ክፍል የሸፈኑት ማቴ.12-18ና ማር.3፡20-8፡38 ያሉት ናቸው። አሥራ ሁለቱ ደቀ መዛሙርት ስለ ኢየሱስ ማንነትና ምን ለማድረግ እንደመጣ ብዙ የተሟሟተ አመለካከትን ከሌሎቹ አይሁዶች ወርሰው ነበር። ደቀ መዛሙርቱ በቅርብ ቀናት ውስጥ በኢየሩሳሌም ለሚፈጸመው ሁኔታ ዝግጁ ሆነው እንዲገኙ ኢየሱስ አስቀድሞ ስለ ራሱ ማንነት ያሣያቸውና ያስተምራቸው ነበር። ኢየሱስ ለሚመሠርተው አዲስ ጉባኤ መሪዎች የሚሆኑት እነርሱ ነበሩ። ስለሆነም ኢየሱስ እነርሱን ለማስተማር ብዙ ጊዜውን አጠፋ።

## ምዕራፍ አሥራ ስምንት - ጥያቄዎች

1. የገሊላውን አገልግሎት በስንት ክፍሎች ልንከፍለው እንችላለን?
2. የመጀመሪያው ክፍል ስንት ድርጊቶች አዝሏል?
3. የመጀመሪያው ክፍል በማርቆስ ወንጌል ውስጥ በየትኛው ስፍራ ይገኛል?
4. በማቴዎስና በሉቃስ ውስጥ የሚመሳሰሉት የትኞቹ ክፍሎች ናቸው?
5. ማርቆስ ከጻፋቸው 17 ድርጊቶች መካከል ሉቃስ የመዘገባቸው ስንት ናቸው?
6. ሉቃስ የሚዘለው የትኛውን ነው?
7. ማርቆስ 1፡39 መግቢያ የሚሰጠን ለየትኛው ክፍል ነው?
8. የገሊላው አገልግሎት 2ኛ ክፍል ምን ተብሏል?
9. የተራራ ስብከት የተሰኘው ክፍል የሚገኘው የት ነው?
10. በማቴዎስ፥ በማርቆስና በሉቃስ ውስጥ ከዚህ የሚቀጥለው ታሪክ ምንድን ነው?

የሚገኙት የትኞቹ ናቸው?

15. 5 የተቃውሞ ታሪኮች የሚገኙት የት ነው?

16. ከገሊላው አገልግሎት መካከል በማቴዎስ ብቻ የሚገኙትና ታላቅ የሆኑት ድርጊቶች የትኞቹ ናቸው?

17. የገሊላውን አገልግሎት 4ኛ ክፍል ምን ብለነዋል?

18. የሜዳ ስብከት የተሰኘው ክፍል የሚገኘው የት ነው?

19. የገሊላውን አገልግሎት 5ኛ ክፍል ምን እንበለው?

20. 5ኛው ክፍል የሚገኘው የት ነው?

21. ለ5ኛው ክፍል አጭር መግለጫ የሰጠው ማን ነው?

22. የአሥራ ሁለቱ መጠራት ታሪክ የሚገኘው በየትኞቹ ወንጌሎች ውስጥ ነው?

# ምዕራፍ 19

## ሦስቱ ወንጌሎች

በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ኢየሱስ ስለ ዘመናት ፍጻሜ የተናገራቸውን ነገሮች የሚይዙትን ማቴ.24-25ን፤ ማር.13ንና ሉቃስ 21ን ለማጥናት እንፈልጋለን። እነዚህ ምዕራፎች ያዘሉትን መልእክት በዮሐንስ ወንጌል ውስጥ አናገኘውም። ይህ ዋጋ ያለው ክፍል ስለሆነ ከሌሎቹ ክፍሎች ጋር ልናያይዘው ይገባል።

በዚህ ክፍል ማቴዎስና ሉቃስ ከማርቆስ ጋር በጣም ይመሳሰላሉ ብለን ትምህርታችንን እንጀምር። ማቴዎስ ስለዚህ ትምህርት ያጠናቀረው ዘገባ ከሁሉ ረዘም ያለ ስለሆነ የማቴዎስን ወንጌል መሠረት አድርገን እንጠቀምበታለን። በማቴዎስ 24፡4-36 ውስጥ 8 ክፍለ ምንባቦች

ውስጥ ሊገባ የሚችለው በማርቆስ 13 በቁጥር 23ና ቁጥር 24 መካከል ነው።

ከስምንቱ ክፍለ ምንባቦች አራተኛው የሚናገረው ስለ ሐሰተኛ ነቢያት ነው (ማቴ. 24፡23-25)። ይህን ክፍለ ምንባብ ማለት አምስተኛውንና ከፍ ብሎ የተጠቀሰውን ማለት አራተኛውን ክፍለ ምንባብ ሉቃስ አልመዘገባቸውም። በማቴ.24፡23-25ና 24፡26-28 ያሉት በሉቃስ 24 ቁጥር 24ና 25 መካከል ይገባሉ። እንግዲህ ማቴዎስ ካቀረባቸው 8 ክፍለ ምንባቦች ማርቆስ አንዱን ሲዘል ሉቃስ ሁለት ይዘላል፤ ከዚያም ሁለቱም የሚዘሉት አምስተኛውን ክፍለ ምንባብ ነው። ከዚህ በቀር አቀራረባቸው በሙሉ ተመሳሳይ ነው።

እነዚህን ስምንት ክፍለ ምንባቦች ከያዘው ከማቴ. 24፡4-6 ስንወጣ ብዙ ልዩነቶችን እናያለን። ወንጌሎች ሁሉ ይህንን ክፍል የሚያጠቃልሉት በተለያየ መንገድ ነው። ማርቆስ የሚያጠቃልለው የማስጠንቀቂያ መልእክት በያዘ ምሳሌ ነው (ማር.13፡33-37)። ሉቃስና ማቴዎስ ይህንን አባባል ቢያውቁትም እንኳ አልጻፉትም።

ወደ ሉቃስ 21 ስንመለከት ደግሞ የተለየ ማጠቃለያ እናገኛለን። ሉቃስ በ21፡34-36 የዘመናትን ፍጻሜ ሳይሆን የኢየሩሳሌምን ጥፋት የሚጠቁመውን የኢየሱስን አባባል ይጠቅሳል። ደግሞ ኢየሱስ በመጨረሻው ሳምንት በኢየሩሳሌም ያደረገውን ሳይጠቅስ ሉቃስ 21፡37-38 በቀጥታ ወደ ሕማማቱ ዘገባ መግባቱን አስተውሉ። ማቴዎስ ከማርቆስና ከሉቃስ ብዙ ስለሚለይ በምዕራፋችን መደምደሚያ ላይ ወደ እርሱ እንመለከታለን።

የማቴዎስ የአጻጻፍ ዘዴ ጽሑፎቹን በሙሉ እርስ በርስ አሰባስቦ ነበር። ስለሆነም በዚህም ክፍል የተጠቀመው በተመሳሳይ መንገድ ነው። ማቴዎስ ከዘመናት ፍጻሜ ጋር ግንኙነት ያላቸውን ስድስት ነጥቦችን አስፍሯል።

በማያያዝ ስለጻፈው ብቻ እነኝህ ነገሮች ሁሉ የተነገሩት በዚያኑ ሰዓት ነው ማለት አንችልም። ይህም ማለት ወንጌላዊው የጊዜውን ቅደም ተከተል ለመከተል አጥብቆ አልሞከረም። ይህን ለማድረግ ስላልሞከረ በግድ እንደዚህ መሆን አለበት ብለን የማስተካከል ሙከራ ማድረግ የለብንም።

ስለ ዘመናት ፍጻሜ የሚናገሩትን እነኝህን አራት ምዕራፎች ማለትም ማቴ.24-25፤ ማር.13ንና ሉቃስ 21ን ስንመለከት በወቅታዊ ቅደም ተከተልነታቸው ከዚህ ጋር ሊያያዙ የሚገባቸውና የዘለልናቸው ሁለት ነገሮች እንዳሉ እንረዳለን። ሆኖም ዓላማችን በቅድሚያ ከፍተኛ የሆኑትን ነገሮች መያዝ ነውና ከዚያ በመቀጠል የቀሩትን ደግሞ በትክክለኛ ቦታቸው ለማስገባት ተመልሰን መመልከት ነው።

ስለ ዘመናት ፍጻሜ ከመነገሩ በፊት የተፈጸሙት እነዚህ ሁለት ነገሮች የሚከተሉት ናቸው፡-

1. በሉቃስ ወንጌል የተመዘገበው የኢየሱስ ጉዞ ዘገባና
2. ኢየሱስ ከመታሠሩ በፊት በኢየሩሳሌም የተፈጸሙት ድርጊቶች ናቸው።

እስካሁን እንደተመለከትነው በአራቱም ወንጌላውያን የተጻፉትን አጠቃላይ የሆኑና በየወቅቱ የተፈጸሙትን ነገሮች ተገንዝበናል። እነርሱም፡- የኢየሱስ መወለድ፥ የመጥምቁ ዮሐንስ አገልግሎት፥ የገሊላው አገልግሎት፤ በኢየሩሳሌም የመጨረሻው ሳምንት፥ የኢየሱስ ሞትና ትንሣኤ ናቸው። የታሪኩን አጠቃላይ ጽንስ አሳብ ከያዝን እያንዳንዱን ድርጊት በዚያ ጽንስ አሳብ ላይ በመመርኮዝ መተርጎም ቀላል ሊሆንልን ይችላል።

እንችላለን?

3. ማርቆስ ሳይጽፍ የዘለለው የትኛውን ታሪክ ነው?

4. ይህ የተዘለለው ታሪክ በማርቆስ ዘገባ ውስጥ በየትኛው ስፍራ መግባት ነበረበት?

5. ሉቃስ ምንና ምንን ትቷል?

6. እነዚህ ሉቃስ የተዋቸው ታሪኮች መግባት የነበረባቸው የትኛው ስፍራ ነበር?

7. ማርቆስ በመደምደሚያው ላይ ያሰፈረው ምንድን ነው?

8. የማርቆስ መደምደሚያ በሌላ ቦታ ይገኛልን?

9. የሉቃስ መደምደሚያ ምንድን ነው?

10. ኢየሱስ ስለነበረው ልማድ አስተያየቱን የሰጠው ወንጌላዊ የትኛው ነው?

11. ማርቆስና ሉቃስ ከመዘገቧቸው ሌላ ማቴዎስ ስንት ነገር ጨምሯል?

12. እስካሁን በጥንቃቄ ያልተመለከትናቸው ሁለት ክፍሎች ምንና ምን ናቸው?

# ምዕራፍ 20

## የዮሐንስ አቀራረብ

ዮሐንስ እንደ ማቴዎስና እንደ ሉቃስ የማርቆስን ጽሑፍ እንዳልተከተለ ደጋግመን ገልጸናል። ዮሐንስ ከእነርሱ በፊት ወይም በኋላ ጽፎ ይሆናል። በየትኛውም ቢሆን ዮሐንስ ስለ ኢየሱስ መምጣት የጻፈው ከሦስቱም ወንጌላውያን ለየት ባለ መንገድ ነው። ይህ ግን ወንጌሉን

1. ኢየሱስ በገሊላ ስለነበረው አገልግሎት ዮሐንስ የሌሎቹን ያህል አልተናገረም። ዮሐንስ ኢየሱስ ገሊላን እንደጎበኘ፥ ተአምራትን እንዳደረገና እንዳስተማረ ያሳየናል። ከገሊላው አገልግሎት ይልቅ ኢየሱስ ከይሁዳ በተለይም በኢየሩሳሌም ባደረገው ድርጊት ላይ በበለጠ አተኩሯል። ኢየሱስ በገሊላ ያደረገውን ሁሉ ዮሐንስ አላወቀም ማለት አንችልም። ምክንያቱም ዮሐንስ በዚያ ወቅት ከኢየሱስ ጋር በገሊላ ነበረ። ነገር ግን ዮሐንስ ለጻፈላቸው አንባቢያን የገሊላው አገልግሎት እንደ ይሁዳውና እንደ ኢየሩሳሌሙ አገልግሎት አስፈላጊ አልነበረም።

2. የዮሐንስ ወንጌል ብዙ ምሳሌ የለበትም። ይህን ስንል ዮሐንስ ምዕራፍ 10 ምሳሌ የለውም ለማለት አይደለም። ዮሐንስ ካቀረባቸው ከኢየሱስ ትምህርቶች ብዙሃኑ ምሳሌ ነክ ናቸው። ሆኖም ከሌሎቹ ወንጌላት ጋር ስናመዛዝናቸው ዮሐንስ የጻፋቸው በሦስቱ ወንጌላት ከሚገኙት ብዙ ምሳሌዎች ጥቂቶቹን ነው።

ዮሐንስ የኢየሱስን ትምህርት ያቀረበው በሁለት ለየት ባሉ መንገዶች ነው፤ ይኸውም በውይይትና በንግግር መልክ ነው። ለምሳሌ በዮሐንስ 6 ላይ ኢየሱስ ከአይሁዶች ጋር እየተወያየ ስለ ሕይወት እንጀራ አስተማራቸው። በዮሐንስ ወንጌል 13-17 ኢየሱስ ለደቀ መዛሙርቱ ረጅም ንግግር በማድረግ ትምህርት ሰጣቸው። ይህ ዐይነት ውይይትና ንግግር በሌሎቹ ወንጌላት ውስጥ በጭራሽ አይገኝም ማለት ሳይሆን እንደ ዮሐንስ በብዛት አላሰፈሩትም ለማለት ነው። ይህ ማለት ደግሞ ወንጌላቱ ከተለያየው አቀራረባቸው የተነሣ እርስ በርስ ይቃረናሉ ማለትም አይደለም።

3. ዮሐንስ ስለ ኢየሱስ የሰጠው አገላለጽ ማቴዎስ፤ ማርቆስና ሉቃስ ከሰጡት የተለየ ነው። የመጀመሪያዎቹ ሦስት ወንጌላት ኢየሱስን ያቀረቡት አይሁዶችን ፊት ለፊት ለመግጠም የሚፈልግ አድርገው ነው። ይህ አመለካከት በዮሐንስ ውስጥ በጣም አነስተኛ ነው።

4. በፍጥናው ጥያቄ ግን የወቅቶቹ ቀደም ተከተል ባይሆን አይቀርም። ሆኖም ሁለት አስፈላጊ ነገሮችን ቀደም ብለን ተመልክተናል። 1. በየወቅቱ የተፈጸሙትን ሁሉንም ነገሮች ለመስጠት የሞከረ ወንጌላዊ የለም። 2. ወንጌላውያኑ ከፍተኛ ትኩረት የሰጡት ምን እንደተፈጸመና ለምን እንደተፈጸመ አማብራራቱ ላይ ብቻ ነበር እንጂ በየወቅቱ የተፈጸሙትን ድርጊቶች በትክክል ቀደም ተከተላቸውን አስይዘው የመጻፍ ትኩረት አልነበራቸውም። በየወቅቱ የተደረጉትን በቅደም ተከተል ተራ ለማስያዝ ዋና ዓላማቸው አልነበረም። በዚህ ርዕስ ሥር የዮሐንስ ወንጌል የሚያነሳቸውን አራት ጥያቄዎች እንመልከት፡-

1. ኢየሱስ ቤተ መቅደሱን ያነጻው መቼ ነበር? በአገልግሎቱ መጀመሪያ እንደሆነ ዮሐንስ አመልክቷል። ሦስቱ ወንጌላውያን ግን በአገልግሎቱ መጨረሻ ላይ አድርገው አስፍረውታል። ለዚህ ጥያቄ ትክክለኛ መልስ ሊሆን የሚችለው ድርጊቱ ሁለት ጊዜ ተፈጽሟል ማለት ነው።

2. ኢየሱስ ከመታሠሩ በፊት የተፈጸሙት የድርጊቶች ቀደም ተከተል እንዴት ነበር? ዮሐንስ አንዳንዶቹን ሲጠቅስ የቀሩትን ደግሞ ማቴዎስ ማርቆስና ሉቃስ ጠቅሰዋቸዋል። እነኝህን አሰባስቦ በትክክለኛ ተራ ማስቀመጥ አስቸጋሪ ከመሆኑም በላይ በተራቸው ማስቀመጡም እጅግ አስፈላጊ አይደለም።

3. ኢየሱስ ለምን ያህል ዓመታት ሰበከ? ሌሎቹ ወንጌላውያን እርግጠኛውን አልገለጹልንም። ዮሐንስ ሦስት ጊዜ የፋሲካ በዓል ማክበሩን ይጠቅሳል። ይህም ሦስቱ ወንጌላውያን ከሰጡት ዘገባ ጋር ይስማማል።

4. ኢየሱስ የመጨረሻውን እራት የቀረሰው መቼ ነበር? በዚህ ጥያቄ ላይ ብዙ መረጃ ስለሌለን ጥያቄውን ለመመለስ በጣም አስቸጋሪ ነው። ብዙዎቹ አይሁዶች ፋሲካን የሚበሉት ዓርብ ነበረ። በአጠቃላይ

ምዕራፍ ሃያ - ጥያቄዎች

1. ዮሐንስ በአጭሩ የዘገበው ክፍል የትኛው ነው?

2. የዮሐንስ አቀራረብ ከሌሎች እንዴት ይለያል?

3. ዮሐንስ ስለ ኢየሱስ ያቀረበው ሥዕል በጣም ልዩ የሆነው በምን ምክንያት ነው?

4. የዮሐንስ ዘገባ በወንጌል ቅደም ተከተል ላይ የፈጠራቸው 4 ጥያቄዎች ምን ምን ናቸው?

5. ዮሐንስ ወንጌሉን በጻፈበት ወቅት የእነማቴዎስን ጽሑፎች አውቆ ይሆን?

6. ኢየሱስ ፋሲካውን የበላው መቼ ነው?

# ክፍል 5

## የእያንዳንዱ ወንጌል ልዩ ባሕርያት

በአምስተኛው የጥናት ክፍላችን እያንዳንዱን ወንጌል በተናጠል እንመለከታለን። እያንዳንዱም አመለካከት በምን መንገድ እንደሚለያዩና እንደሚስማሙ ለማወቅ እንሞክራለን።

# ምዕራፍ 21

## ወንጌላቱ የመነጩት ከኢየሱስ ነው

የኢየሱስን መምጣት ትርጉም በመስጠት ሐዋርያት ተቀዳሚ ሥልጣን ያላቸው መሆኑን አስቀድመን ተመልክተናል። ከዚህም በመነሣት ይህንን ነጥብ እንዳናጋንን መጠንቀቅ አለብን። አንዳንድ ምሁራን ይህንን በማጋነን ሐዋርያት ወንጌልን እንዳመነጩ አድርገው ይናገራሉ። ይህ የተሣሣተ አመለካከት ነው። ጳውሎስ በ55 ዓ.ም. በቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን ላሉ ምእመናን ሲጽፍ የወንጌልን ጽንስ አሳብ ከሌሎች እንደተቀበለው በሁለት

ኢየሱስ ስለ ራሱ በተናገረው ላይ የተመሠረተ ነው። ጳውሎስ የኢየሱስን መልእክት ለውጦአል ማለት የተሳሳተ አመለካከት ነው። በወንጌል ውስጥ የምናገኘውን ትርጉም በጳውሎስ መልእክቶች ውስጥ ሙሉ በሙሉ ተመሳሳይ ሆኖ እናገኘዋለን። ወንጌልን በምታነቡበትና በምታስተምሩበት ጊዜ በጳውሎስ መልእክትም ውስጥ ጎን ለጎን የሚሄደውን ክፍል ፈልጉ። ከዚህ ቀጥለን በ8 ነጥቦች የምናጠቃልለው ወንጌል የመጣው በቀጥታ ከኢየሱስ ከራሱ መሆኑንና የተመሠረተውም በብሉይ ኪዳን ላይ እንደሆነ ነው።

የመጀመሪያዎቹ ሰባኪዎች የኢየሱስን ማንነት የገለጹት እንዴት ነበር? ብለን ራሳችንን መጠየቅ ይረዳናል። ኢየሱስ ስለራሱ ማንነት በቃልና በተግባር ለማስረዳት ብዙ ጊዜ መውሰዱን ቀደም ብለን ተመልክተናል። የመጀመሪያዎቹ ሰባኪዎች ምን ይላሉ?

በሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ ውስጥ ለዚህ ጥያቄ ትክክለኛ መልስ እናገኛለን። የመጀመሪያዎቹ ሰባኪዎች ስለ ኢየሱስ ማንነት እንዴት እንደሰበኩ በቅርብ ለመመልከት የሚያስችሉን ሦስት ረጃጅም መልእክቶች በሐዋርያት ሥራ ውስጥ እናገኛለን። እነርሱም:-

1. በበዓለ ኀምሳ ቀን ጴጥሮስ የሰበከው ስብከት (የሐዋ.2፡14-36)።

2. ጴጥሮስ በቆርኔሌዎስ ቤት ለተሰበሰቡ አይሁዶች የሰበከው ስብከት (የሐዋ. 11፡34-43)።

3. ጳውሎስ በገላትያ የሰበከው ስብከት (የሐዋ. 13፡16-41)።

በሐዋርያት ሥራ ውስጥ ሌሎችም ስብከቶች ስላሉ እነርሱን በማመሳከር የተጣመረ መልስ ለማግኘት እንችላለን። እነኝህን ስብከቶችና በወንጌላት ውስጥ የሚገኘውን የኢየሱስን መልእክት በማጥናት

ወይም አቀራረቡ የተሟላ ባይሆን [illegible] የሚከተሉት 8 ነጥቦች በወንጌሎችና በሐዋርያት ሥራ ውስጥ ያሉትን አስፈላጊ ገለጻዎች ያሰባስባሉ ለማለት እንችላለን።

1. የእግዚአብሔር የመጎብኛ ሰዓት ቀርቧል የሚለው በብሉይ ኪዳን ውስጥ የተሰጠው የተስፋ ቃል በተግባር ላይ ውሏል።
2. ሁሉም የሚያውቁት የናዝሬቱ ኢየሱስ መሢሁ ነው።
3. ኢየሱስ ሞቷል ተቀብሮማል።
4. ከሙታን ተነሥቷል።
5. ወደ ሰማይ ዐርጓል።
6. ከተከታዮቹ ጋር አብሮ እንዲሆን መንፈስ ቅዱስን ልኳል።
7. ወደ ምድር ተመልሶ ይመጣል።
8. በስሙ የሚታመኑ አዲስ ሕይወትን ያገኛሉ።

እነዚህ ሁሉ ነጥቦች በሐዋርያት ሥራ ውስጥ እንደሚገኙ ሁሉ በወንጌሎችም ውስጥ ይገኛሉ። ጥንት ክርስቲያኖች በሙሉ የመሰከሩለት ዘገባ ይህ ነው።

ምንም እንኳን ስለ ኢየሱስ ወደ ዓለም መምጣት የሚገልጹት አስፈላጊ ነጥቦች እነዚህ ቢሆኑም በእነዚህ አጠቃላይ ነጥቦች ላይ እያንዳንዱ ጸሐፊ መጠነኛ የሆነ ልዩ ልዩ አመለካከትን ይሰጠናል። እያንዳንዱ ወንጌል በአጠቃላይ አመለካከት የሚሰጠውንም ሆነ በተናጠል የሚሰጠውን ነጥቦች መማር ያስፈልገናል።

## ምዕራፍ 21- ጥያቄዎች

1. ጳውሎስ 1ኛ ቆሮንቶስን የጻፈው መቼ ነበር?

5. የሚገኙት የት የት ነው?

6. በእያንዳንዳቸው ውስጥ ስንት ዋና ዋና ነጥቦች ይገኛሉ?

7. በወንጌሎች ውስጥ ከምናገኘው ትምህርት ጋር ስናስተያያቸው ምን እንመለከታለ?

8. እያንዳንዱ ወንጌላዊ የሚያቀርብልን ዘገባ ምንድን ነው?

# ምዕራፍ 22

## ማርቆስ

የማርቆስ ወንጌል ከአራቱ ወንጌላት ይልቅ አጭር ነው፤ ነገር ግን የማቴዎስን ወንጌል ዋና ዋና ነጥቦች ብቻ የያዘ ነው ማለት በፍጹም ስሕተት ነው። ምንም እንኳን አጭር ቢሆንም የኢየሱስን ሥራ ልዩ በሆነ ሁኔታ አቅርቦታል። ምንም እንኳን በማርቆስ ውስጥ የሌለውን ብዙ ነገሮች ማቴዎስ ቢጽፍም በአንዳንድ ዘገባ ላይ ማርቆስ ከማቴዎስ ይልቅ ብዙ ዝርዝሮች አቅርቧል። ማርቆስ በዘገባው ላይ በዓለም ውስጥ በመልካምና በመጥፎ ነገሮች መካከል ስለሚደረገው ውጊያ መደጋገም ላይ ትኩረት ሰጥቶአል። በጥሩና በመጥፎ መካከል የሚካሄደውን ውጊያ በመደጋገም ጠቁሟል። ኢየሱስ በምድር ላይ በነበረበት ወቅት የተካፈላቸው እነዚህ ትግሎች በብዙ ታሪኮች ተጠቁመዋል።

ክፋት ምንጭ የሌለው ኃይል ሳይሆን አመንጪው ሰይጣን መሆኑን ማርቆስ ያመለክታል። በምድረ በዳው ፈተና ተጀምሮ በመስቀል ሞት ላከተመው ውጊያ ማርቆስ ከፍተኛ ትኩረት ሰጥቶታል። በማንኛውም ውጊያ ውስጥ ሰይጣን መሸነፉ በማርቆስ ወንጌል ውስጥ ግልጽ ሆኖ ቀርቧል። ታላቁና ዘለቄታ ያለው የሰይጣን ሽንፈት በአማንያን ሕይወት ውስጥ የተፈጸመ ነው።

የተለያዩ ምሳሌዎች ይገኛሉ። ከእነዚህ ከ70 ምሳሌዎች ውስጥ ማርቆስ የተጠቀመው 18 ብቻ ነው። ይኸውም 1/4ኛ ብቻ መሆኑን አስተውሉ። ማርቆስ ያተኮረው ኢየሱስ ካስተማራቸው ትምህርቶች ይልቅ በፈጸማቸው ድርጊቶች ላይ ነው።

በወንጌላቱ ውስጥ 35 የተለያዩ ተአምራትን እናገኛለን። ከ35ቱ ውስጥ ማርቆስ 18ቱን አስፍሯል! ይህም ግማሹን ማለት ነው። ይህ የሚያመለክተን ማርቆስ ትኩረት የሰጠው ኢየሱስ በክፉት ግፊት ላይ ያለውን ኃይል ነው። እነኝህን ተአምራት በምታነቡበትና በምታስተምሩበት ጊዜ ኢየሱስ ምን ማድረጉ እንደሆነና ለምን እንዳደረገው ራሳችሁን ጠይቁ።

ማርቆስ ተአምራትን የተጠቀመበት ዘዴ በዚህ ምዕራፍ መጀመሪያ ያቀረብነውን አሳብ ያብራራል። ማርቆስ ትኩረት ከሰጠባቸው ዋና ዋና ነገሮች አንዱ ሰይጣን የእግዚአብሔር ልጅ በሆነው በኢየሱስ መሸነፉን ነው።

የተሰበሰበው ሕዝብ ያሳየውን አጸፋ በማርቆስ ወንጌል ውስጥ ብዙ ጊዜ ተደጋግሞ ተጽፎ እናገኛለን። የተሰበሰበው ሕዝብ ኢየሱስ ያደረገውን ሲመለከት የሰጠውን መልስ ማርቆስ 23 ጊዜ ጽፎታል። ማርቆስ ከትምህርት ይልቅ የተግባር ወንጌል መሆኑን የሚገልጹ ሌላ ሁለት ነገሮች አሉን። «ወዲያውኑ» ተብሎ የተተረጎመውን የግሪኩን ቃል ኡቱስ ማርቆስ 42 ጊዜ ተጠቅሞበታል። እንዲሁም ድርጊቱ የሚቀጥል መሆኑን በሚገልጹ የግሪክ ግሦች ተጠቅሟል።

እንዲሁም የማርቆስ ወንጌል ለኢየሱስ ሥቃይና መከራ ትኩረት የሚሰጥ ነው። ይህ ርእስ በተደጋጋሚ በብሉይ ኪዳን የሚገኝ መሆኑን ቀደም ብለን ተመልክተናል። ምናልባት በዚህ ምክንያት ማርቆስ

መንግሥቱንም ለመመሥረት ዝግጅት ማድረጉ እንደተከናወነለት ማቴዎስ ያሳየናል። ማርቆስ ደግሞ ኢየሱስ የኢሳይያስ ምዕራፍ 53 ን ትንቢት አሟልቶ እንደፈጸመ ያሳያል። በመከራው ሕዝቡን የሚዋጀው እርሱ ኢየሱስ ነው። ደኅንነት የሚገኘው በሥቃይ አማካይነት ነው የሚለውን የማርቆስ ወንጌል ርእስ ለመረዳት በጣም ሊያዳግተን ይችላል። ኢየሱስ ፍጹም ሰው መሆኑን ሉቃስ ያሳየናል። ኢየሱስ ከኃጢአት በቀር በሁሉም ነገር ልክ እኛን መስሎ ስለመጣ ወንድሞቹ ብሎ ይጠራናል። ዮሐንስ ደግሞ ኢየሱስን ወደ አብ የሚያደርሰው መንገድ መሆኑን በሚገባ አድርጎ አቅርቦታል። ኢየሱስ እግዚአብሔር ስለሆነ ፍጹም አዳኝ ነው።

ለአጠቃላይ ትርጉም ማርቆስ ያደረገው አስተዋጽኦ በጣም ዋጋ ያለው ነው። እያንዳንዱ ወንጌላዊ የተለያየ አስተዋጽኦ መስጠቱን ከተረዳን አራቱን ወንጌላት በማቀናጀት አንድ ወጥ ለማድረግ ይቀለናል።

## ምዕራፍ ሃያ ሁለት - ጥያቄዎች

1. ማርቆስ በወንጌሉ የሚገልፀው የትኛውን ዓይነት ውጥረት ነው?
2. ከከፋት አንጻር የኢየሱስ አቋም ምንድን ነው?
3. ኢየሱስ ከተናገራቸው 70 ምሳሌዎች ስንቶቹ በማርቆስ ውስጥ ይገኛሉ?
4. ከ35ቶቹ ተአምራት መካከል ስንቶቹ በማርቆስ ውስጥ ይገኛሉ?
5. ማርቆስ ትኩረት የሚሰጠው በምን ላይ ነው?
6. ማርቆስ የሚያመለከተው የትኞቹ ትንቢቶች መፈጸማቸውን ነው?

ኢየሱስ ያሟላዋል። በብሉይ ኪዳን ውስጥ ለሚገኙት ውስብስብ ጥያቄዎች ሁሉ መልስ ይሆናቸዋል። በብሉይ ኪዳን ውስጥ ያሉት የጨለሙ ስፍራዎች ግልጽ እንዲሆኑ እርሱ በብርሃን መጣ። ብሉይ ኪዳንና አዲስ ኪዳን የተገጣጠሙ ሳይሆኑ በኢየሱስ መምጣት አንደኛው ሌላውን የሚያብራራ መሆኑን ማቴዎስ ያመለክታል።

በማቴዎስ ወንጌል ውስጥ ኢየሱስ ስምንት ጊዜ «የዳዊት ልጅ» ተብሎ ተጠርቷል። እግዚአብሔር ለዳዊት መሢሁ ማለትም የተቀባው ከቤተሰብህ ይነሣል ብሎ ቃል ኪዳን ገብቶለታል (2ኛ ሳሙ. 7፡14)። ከዚህ በላይ በሚገኘው ጥቅስ ውስጥ «ልጅ» ማለት «ወራሽ» ማለት ነው። ማቴዎስ «የዳዊት ልጅ» የሚለውን ቃል በመጠቀም ኢየሱስ የብሉይ ኪዳንን ተስፋ ቃልና ትንቢቶች ወራሽ መሆኑን አበክሮ ይገልጻል። ሆኖም ግን በብሉይ ኪዳን ውስጥ የተነገሩለት ትንቢቶች ከጊዜ በኋላ መፈጸማቸውን ለማመን ለአይሁዶች አስቸጋሪ ነገር ሆነባቸው። መሢሁ ሲመጣ ከሮም ቅኝ ግዛት ነጻ አውጥቶአቸው እሥራኤልን አዲስ መልክ ይሰጣታል በሚል አስተሳሰብ የተሞሉ ስለነበሩ መንፈሳዊ አገልግሎቱን ለመቀበል በጭራሽ አልተቻላቸውም።

ኢየሱስ መሢሕ እንደመሆኑ ለዳዊት የተሰጠውን የተስፋ ቃል ወራሽ ስለሆነ አዲስ መንግሥት ያቋቁማል። እንደ ገዢ አድርገው የሚቀበሉትን ሕዝቦች ለማሰባሰብ መጣ። የማቴዎስ ወንጌል እምብርት ይህ ነው። አዲስና የተለየ ሕይወት እንዲኖሩ ኢየሱስ ለእነዚህ ሰዎች የሚያስፈልጋቸውን ሁሉ አቅርቦላቸዋል።

ዝቅ ብለው የተዘረዘሩት አምስት ንግግሮች ኢየሱስ ያሰባሰባቸውን ማኅበሮች ለማስተማር የተጠቀመባቸው ናቸው።

3. ማቴዎስ 13 የኢየሱስ መንግሥት እንዴት እንደምትመሠረት ያሳየናል። አይሁዶች በጠበቁት አንጻር ሲታይ በጣም ልዩ ስለሆነ ኢየሱስ መንግሥቱ እንዴት እንደምትመሠረት በዝርዝር ማስረዳት ነበረበት።

4. ማቴዎስ 18 የአዲሱ ኅብረተሰብ ሕይወት እንዴት መሆን እንደሚገባው በዝርዝር ያስረዳል። ይህም ኢየሱስ ተከታዮቹ እንዴት በአንድነት መኖር እንደሚገባቸው ያስተማረበት ክፍል ነው።

5. ማቴዎስ 23-25 ኢየሱስ አገልግሎቱን እንዴት አድርጎ እንደሚያጠቃልል ይነግረናል። የመጨረሻው ዘመን እንዴት እንደሚመጣ ማወቁ ለእኛ አስፈላጊ ነው። በእነዚህ ሦስት ምዕራፎች ኢየሱስ ስለ ኢየሩሳሌምና ስለ ዓለም ማለትም ስለ ሁለቱም ተናግሯል።

ከአራቱ ወንጌላት መካከል ማቴዎስ ብቻ ቤተ ክርስቲያን የሚለውን ቃል ተጠቅሞበታል። በማቴዎስ ወንጌል ውስጥ ሁለት ጊዜ ተጠቅሷል (16፡18፤ 18፡15-17)። ቃሉ አዲስ አይደለም (የሐዋ. 7፡38)። እንዲሁም በብሉይ ኪዳን ውስጥ ለሚገኙ ለእግዚአብሔር ምርጥ ሰዎች የተሰጠ የተለመደ ቃል አይደለም።

ጳውሎስ ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ዳግም ምጽአት ሲናገር የሚጠቀምበትን የግሪክ ቃል ፓሩሲያን ከወንጌላውያን መካከል የተጠቀመበት ማቴዎስ ብቻ ነው። ይህ ቃል በማቴዎስ ወንጌል ውስጥ 4 ጊዜ ተጠቅሷል (ማቴዎስ 23 ቁጥር 3፥ 27፥ 37ና 49)። ግሪኮች ይህንን ቃል የሚጠቀሙበት አንድ ባለሥልጣን በይፋ ወደ ከተማ ሲገባ ለመግለጽ ነው።

2. የክርስትናን ትርጉም ለሌሎች መንገር እንዲችሉ ለአዳዲስ ክርስቲያኖች መመሪያ ለመስጠት ስለፈለገ ነው።

3. ያለምንም መጠራጠር መመስከር እንዲችሉ አማንያኑን ማደፋፈር አስፈላጊ ስለሆነ ነው።

ምንም እንኳን የማቴዎስ ጽሑፍ በማርቆስ በሉቃስና በዮሐንስ ውስጥ በብዛት ቢገኝም የሚሰጠው ትኩረት ይለያያል። ማቴዎስ የሚሰጠውን ልዩ የሆነ ተሳትፎ በሚገባ መረዳት ከቻልን የእርሱን መጽሐፍ ይበልጥ መተርጎም እንችላለን።

## ምዕራፍ ሃያ ሦስት - ጥያቄዎች

1. ማቴዎስ ኢየሱስን የሚያቀርበው እንዴት አድርጎ ነው?

2. የዳዊት ልጅ የሚለው በማቴዎስ ወንጌል ውስጥ ስንት ጊዜ ይገኛል?

3. ማቴዎስ የዳዊት ልጅ በሚለው ቃል የሚጠቀመው ለምንድን ነው?

4. የማቴዎስ አምስት ንግግሮች የሚገኙት የት ነው?

5. እያንዳንዱ ንግግር ተደርጎ የነበረው ለማን ነበር?

6. በማቴዎስ ውስጥ ቤተ ክርስቲያን የሚለው ቃል የሚገኘው በየትኛው ስፍራ ነው?

7. ማቴዎስ በዚህ ቃል ሲጠቀም ምን አስቦ ነው?

8. በማቴዎስ ወንጌል ውስጥ ፓሩሲያ የሚለው የግሪክ ቃል የሚገኘው በየትኛው ስፍራ ነው?

9. ፓሩሲያ የሚለው ቃል ምን ይጠቁማል?

10. ማቴዎስ ወንጌሉን ሲጽፍ ምን ምን ዓላማዎች ይዞ ይሆን?

መንፈሳዊ ፍላጎት ካልተሟላላቸው የሐኪሞች ሥራ ብቻውን ምንም እንደማይረዳ ያውቃል።

ሰዎች በማንኛውም ደረጃ ያላቸውን ግንኙነት የሚያበላሸው ኃጢአት መሆኑንም ያውቃል። በሉቃስ ወንጌል ውስጥ ኢየሱስ ከወንዶች፥ ከሴቶች፥ ከሽማግሌዎችና ከወጣቶች ጋር እየተገናኘ የሚጎድላቸውን ሁሉ ሲያሟላላቸው እንመለከታለን። ኢየሱስ ከሰይጣን ይልቅ እጅግ ኃያል መሆኑንና የተለያዩ ሰዎችን ችግር የሚረዳ መሆኑ ተገልጿል። ኢየሱስ በሉቃስ ወንጌል ውስጥ እንደ ሐኪም ሆኖ ኃጢአት ያወደመውን ሕይወታቸውን ሲፈውስ እንመለከታለን።

ሉቃስ እንደ ማቴዎስ የብሉይ ኪዳንን አስፈላጊነት አበክሮ አይገልጽም። እንዲሁም እንደ ማርቆስ ኢየሱስ ከክፉት ጋር ያደረገውን ውጊያ አብዝቶ አያወሳም። ይሁን እንጂ ስለ ኢየሱስ የሚሰጠው ገለጻ ከእነርሱ በጣም ለየት ያለ አይደለም። እርሱ ያደረገው ያንኑ መልእክት በተለየ አመለካከት ማብራራትና መግለጽ ብቻ ነው።

ምንም እንኳን ወንጌላውያኑ ሁሉ «ለመዳን» የሚለውን ግሥ ቢጠቀሙም «አዳኝ» የሚለውን ስም የተጠቀሙበት ሉቃስና ዮሐንስ ብቻ ናቸው (ሉቃስ 1፡47፤ 2፡11ና ዮሐንስ 4፡42)። በተጨማሪም ሉቃስ «ለማዳን» የሚለውን ግሥ ከብዙዎቹ ወንጌላውያን የበለጠ ተጠቅሞበታል። ይህም ሉቃስ የኢየሱስን አዳኝነት አበክሮ እንደሚገልጽ ያመለክታል።

የሉቃስን መጽሐፍ ስታነቡ ኢየሱስ ብዙ የተለያዩ ሰዎችን ለማግኘት ከመንገዱ ወጥቶ አቅጣጫውን እንዴት እንደለወጠ የሚያሳዩ ብዙ ምሳሌዎችን ለመቁጠር ትችላላችሁ። ማቴዎስ ኢየሱስ ለአይሁዶች መመስከሩን አበክሮ ይገልጻል፤ ነገር ግን ኢየሱስ ከአይሁዶችም ውስጥ

በተለየ ሁኔታ ሊረዳቸውም ፈቃደኛ ነበረ። እነርሱም ይፈልጉታል፥ እርሱም ሄዶ ሊረዳቸው ዝግጁ ነበረ።

ከወንጌላውያኑ ሁሉ የኢየሱስን ታሪክ ከዓለም ታሪክ ጋር ለማያያዝ የሞከረው ሉቃስ ብቻ ነው። ይህ በበለጠ ጎልቶ የሚታየው በሉቃስ 3፡1-3 ውስጥ ነው። በዚህ ጥቅስ ውስጥ ሉቃስ የኢየሱስን መወለድ በአይሁድ ዓለም ውስጥ በወቅቱ ከነበሩት የተለያዩ ሁኔታዎች ጋር ያዳምረዋል።

እንዲሁም ሉቃስ ስለ ሄሮድስ ቤተሰብ የተለየ ስሜት እንደነበረው በሉቃስ ወንጌል ውስጥ እናገኛለን። ሉቃስ በሄሮድስ ቤተ መንግሥት ውስጥ የሚካሄደውን ነገር በቅርብ የሚያውቁና የሚነግሩት ጓደኞች ያሉት ይመስላል። ስለሆነም በኢየሱስ ዘመን በይሁዳ የሚኖሩ የአይሁዶች ታሪክ ሙሉ በሙሉ ከወንጌል ያልተለየ መሆኑን ሉቃስ ያመለክተናል።

በብዙ የብሉይ ኪዳን መጻሕፍትም ተመሳሳይ አመለካከትን እናገኛለን። ከሌሎቹ ሕዝቦች ታሪክ አንጻር እግዚአብሔር ከራሱ ሕዝብ ጋር መሥራቱን እንረዳለን። እግዚአብሔር በራሱ ሕዝብ መካከል ያደረገው ሥራ ጥቂት ሰዎች ብቻ እንዳያውቁት በምስጢራዊ ስፍራ የተፈጸመ አይደለም።

ሉቃስ ከሌሎቹ ወንጌሎቹ የበለጠ የመንፈስ ቅዱስን ሥራ አጉልቶ የሚያሳይ ወንጌል ነው። ሉቃስ በተለይም መንፈስ ቅዱስ በራሱ በኢየሱስ ሕይወት ውስጥ የሚሠራውን ሥራ አጉልቶ ያሳያል። ይህን ተግባራዊ ከሆን የክርስትና ሕይወት ጋር በማያያዝ ሉቃስ አቅርቦታል። ይህም ፍጹም ጎልቶ ሊታይ የሚችለው መንፈስ ቅዱስ በእግዚአብሔር ሕዝቦች ልብ ውስጥ መሥራት ሲጀምር ነው።

ጽፏል፤ ሆኖም ከዚህ በላይ የተጠቀሱት ነጥቦች ሉቃስን ከሌሎቹ የተለየ ያደርገዋል።

## ምዕራፍ ሃያ አራት - ጥያቄዎች

1. ኃጢአት በሰዎች መካከል ምን አድርጓል?

2. ሉቃስ በወንጌሉ ስለዚህ ብልሽት ምን ያመለክታል?

3. መድኃኒት በሚለው ቃል ሉቃስ ስንት ጊዜ ተጠቅሞበታል? የት?

4. ሉቃስ ትኩረት የሚሰጠው በምን ላይ ነው?

5. ሉቃስ የዓለምን ታሪክና የመጽሐፍ ቅዱስን ታሪክ ምን አድርጓል?

6. ሉቃስ 3፡1-3 ምን ያሳየናል?

7. ሉቃስ ትኩረት የሚሰጠው በምንና በምን ላይ ነው?

# ምዕራፍ 25

## ዮሐንስ

ሰው ስላለፈው፥ ስለሚመጣውና አሁን ስላለው ነገር የማሰብ ችሎታ ስላለው፥ ክፉና ደጉን በአእምሮው ሊያመዛዝን ስለሚችልና የራሱን ምርጫ መከተል ስለሚችል ሰው ሊዛመድ የሚችለው ከእንስሳት ዓለም ጋር ሳይሆን ከእግዚአብሔር ጋር ነው። ይሁን እንጂ ሰው ከእግዚአብሔር ጋር ሰላም እንደሌለው የታወቀ ነው። እንዴት ሰላምን ሊያገኝ ይችላል? ኢየሱስ በዮሐንስ ወንጌል ውስጥ የእግዚአብሔር መገለጥ ወይም የእግዚአብሔር መስታወት ተብሎ ይጠራል። ኢየሱስ በሁለቱም መካከል ስለቆመ እግዚአብሔርንና ሰውን ለማስታረቅ ይችላል። ይህ አሳብ በሁለት የግሪክ ቃላት ተገልጿል፡- እነርሱም ሎጎስና ሜርኤክስ የሚሉ ናቸው። ዮሐንስ በወንጌሉ ውስጥ በመደጋገም ሎጎስ የነበረው በኋላም ሜርኤክስ የሆነው ኢየሱስ እንዴት ሰላምን፥ አንድነትንና ይቅርታን እንዳመጣ

ጥቅሶች ኢየሱስ ስለራሱ የተናገረውን ሙሉ በሙሉ አያጠቃልሉም። የዮሐንስን ወንጌል ስታነቡና ስታጠኑ ኢየሱስ ስለ ራሱ ማንነት የተናገረባቸውን ጊዜያት ተመልከቱ። በአዲስ ኪዳን ውስጥ ኢየሱስ ስለ ራሱ የተናገራቸውን ማስረጃዎች ስናስተውል እነኝህ ልዩ የሆነ ክብደት ያላቸው መሆኑን እንገነዘባለን።

የዮሐንስ ወንጌል በኢየሩሳሌም ዙሪያ ያተኮረ መሆኑን ቀደም ብለን ተመልክተናል። ዮሐንስ ኢየሱስ በገሊላ ያደረገውን በቸልታ አልተመለከተውም፤ ነገር ግን ብዙውን ክፍል የሰጠው ኢየሱስ በኢየሩሳሌም ለፈጸመው ሥራ ነው። ለምን? ይህንን ስላደረገ አሁን የይሁዳ እምነት መሪዎች የኢየሱስን ማንነት አናውቅም። ኢየሱስ ትምህርቱን የሰጠውና ተአምራቱን ያደረገው በምስጢር ገሊላ ውስጥ ነው፤ ወይም በገሊላ አውራጃ የሚገኙትን መሃይማን ገጠሬዎች አታለለ ለማለት አይችሉም።

እንዲሁም ዮሐንስ አይሁዶች የኢየሱስ ጠላቶች መሆናቸውን በግልጽ አመልክቷል። ይህንን ነጥብ በማጋነን ኢየሱስ ከአይሁዶች ጋር ለመዋጋት እንደተነሣሣና ባገኘውም አጋጣሚ ሁሉ እንደተጠቀመበት አድርገን እንዳናስተምር ወይም እንዳናስብ መጠንቀቅ አለብን። በየትም ስፍራ ኢየሱስና አይሁዶች ሲገናኙ ኢየሱስ የሚጠይቃቸው ይህንን ነበር፡- እንደ መሢህ አድርጋችሁ ተቀብላችሁኛልን? የአይሁድ መሪዎች ግን ምን ጊዜም ቢሆን አልተቀበሉትም።

የዮሐንስን ወንጌል በምታነቡና በምታጠኑበት ጊዜ ሁሉ ዮሐንስ ብሉይ ኪዳንን እንዴት እንደተጠቀመበት ለማወቅ ጠለቅ አድርጋችሁ ተመልከቱ። ማቴዎስ ብሉይ ኪዳንን እንዴት እንደተጠቀመ ቀደም ብለን አስተውለናል። እርሱ ጥቅሶችን ከብሉይ ኪዳን ይጠቅሳል። ጥቅሶቹ ሲያጋጥሙን ትክክለኛ ትርጉማቸውን ለማግኘት ታሪኩ የተገኘበትን ክፍለ

ጊዜ ኢየሱስ እንዴት የብሉይ ኪዳንን አሳቦችና ትምህርቶች ወስዶ እንደተጠቀመባቸው በጥንቃቄ ለማስተዋል ሞክሩ። ኢየሱስ የብሉይ ኪዳንን ትምህርት እንዴት ወደ ራሱ ትምህርት እንዳስገባ ለማወቅ አንዳንዴ ማብራሪያ ወይም የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጓሜ መጻሕፍትን መመልከት ይጠቅማል። እነዚህን ክፍለ ምንባቦች ከዮሐንስ ወንጌል ስታጠኑ ማቴዎስ ብሉይ ኪዳንን ከተጠቀመበት መንገድ ጋር አመዛዝኑ።

«የዘላዓለም ሕይወት» የሚለው አባባል በዮሐንስ ወንጌል ውስጥ የተለየ ትርጉም አለው። የዘላዓለም ሕይወት አሁን ለአማንያን የተሰጠ የእግዚአብሔር ሕይወት ነው። የኢየሱስ መንግሥት መመሥረቷን፥ እያደገች መሆኗንና የመጨረሻ መገለጥን የምትጠብቅ መሆኑን ቀደም ብለን ተመልክተናል። እነዚህ ሦስቱ እውነት ናቸው፤ አይቃረኑም። ማቴዎስ 24-25፤ ማርቆስ 13ና ሉቃስ 21 በመጨረሻው ነጥብ ላይ ትኩረት ይሰጣሉ።

ዮሐንስ አበክሮ የሚያብራራው የመጀመሪያውን ነው። የዘላዓለም ሕይወት ወደፊት የምንቀበለው ነገር አይደለም። ኢየሱስ እርሱን ለሚከተሉና የእግዚአብሔር ቤተሰብ አባል ሊሆኑ ለሚፈልጉት ሁሉ የዘላዓለምን ሕይወት ሰጥቷል። የዘላዓለም ሕይወት ማለት የእግዚአብሔርን መንግሥት መውረስ ነው። የዘላዓለም ሕይወት ማለት ዳግም መወለድ ነው። የዘላዓለም ሕይወት ማለት ከእግዚአብሔር ጋር ሰላምን መፍጠር ነው። የዘላዓለም ሕይወት ማለት የኃጢአትን ስርየት መቀበል ነው።

## ምዕራፍ ሃያ አምስት - ጥያቄዎች

1. ኢየሱስ መካከለኛው መሆኑን ለመግለጽ ዮሐንስ የተጠቀመባቸው ሁለት ቃላት ምንና ምን ናቸው?

2. በዮሐንስ ወንጌል በተደጋጋሚ የሚገኘው ነጥብ ምንድር ነው?

7. ዮሐንስ ስለ ኢየሱስ መንግሥት የሚያቀርበው የትኛውን ገጽታ ነው?

8. በማቴ.24-25፤ ማር.13ና ሉቃስ 21 ላይ ትኩረት የተሰጠው ለየትኛው ገጽታ ነው።?

# ክፍል ስድስት

## ዘገባዎችን የማዋሐድ አሳብ

በአራቱም ወንጌሎች ውስጥ ምንም ቅራኔ የለም። አራቱም እንዲሉ ማጥናት ያስፈልገናል። አራቱም አንድ ላይ ካልተሰበሰቡ በቀር ታሪኩን አናገኝም ብለን ለማዋሐድ መሞከር ደግሞ አስፈላጊ አይደለም።

# ምዕራፍ 26

## ልዩነት አስፈላጊ ነው

በ170 ዓ.ም. አካባቢ ታቲያን የተባለ ሰው አራቱን ወንጌላት በሙሉ አዋሕዶ አንድ መጽሐፍ ለማድረግ ወሰነ። የኢየሱስን ታሪክ ከመዘገቡ አራት መጻሕፍት ይልቅ አንድ ብቻ ለማስገኘት ፈለገ። ይህ ብዙ የሚነሱ ጥያቄዎችን አስወግዷል። ያቀነባበረው መጽሐፍ ዲያተሣሮን በመባል ይጠራል። የተጻፈውም በሶርያ ቋንቋ ነው። የሶርያ ቋንቋ ተናጋሪ ቤተ ክርስቲያናት መጽሐፉን በአራቱ ወንጌላት ምትክ ተቀበሉት። ተቀብለው ለ400 ዓመታት ከተጠቀሙበት በኋላ አራቱን ወንጌላት በመምረጥ መጽሐፉን ካዱት።

በዚያንም ወቅት ቢሆን ሌሎቹ አብያተ ክርስቲያናት ይህንን ዲያተሣሮን የተባለውን መጽሐፍ በወንጌላቱ ምትክ አድርገው አልተቀበሉትም ነበር። ወንጌላትን በሙሉ በአንድ ላይ አዋሕዶ ለመጻፍ ዲያተሣሮን የመጀመሪያውም የመጨረሻውም ሆነ። ከዚያ በኋላ ማንም ቤተ ክርስቲያን ይህንን ለማድረግ አልፈለገም።

ይችላሉ። ስለዚህ ወንጌል ማለት የአራት ዘገባዎች አጠቃላይ ድምር ወይም ውሕደት አይደለም። በእርግጥም አራቱን ወንጌላት በአንድ ላይ ማዋሐዳችን ምንም አይጠቅመንም። ወንጌላውያኑ እያንዳንዳቸው የኢየሱስ ክርስቶስን መምጣት የሚናገሩ ነጥቦችን በተለያየ መንገድ አቅርበዋል። እያንዳንዱ ጽሑፍ የግሉ የሆነ ባሕርይ አለው። ትልቅ ግምት የምንሰጣቸው ተመሳሳይ ለሆኑት ምንባቦች ሳይሆን ልዩነትን ለሚያሳዩን ክፍሎች ነው። አራቱም ዘገባዎች ያስፈልጉናል። ዘገባዎቹንም ልናመዛክራቸው እንችላለን፤ ሆኖም አንዱ ከሌላው ይበልጣል በሚል ስሜት አይሁን። አራቱም እኩል ጥቅም አላቸው። እያንዳንዳቸው ያስፈልጉናል።

አራቱን ዘገባዎች ስናመሳክር የምናገኛቸውን ሦስት የታወቁ ልዩነቶችን እንመልከት።

1. ምሳሌዎች፡- የዮሐንስ ወንጌል እንደ ሌሎቹ ወንጌላት ምሳሌያዊ ጽሑፎችን አልያዘም። ነገር ግን የዮሐንስን ወንጌል ብቻ በመጥቀስ ኢየሱስ በምሳሌ አላስተማረም ብንል ስሕተተኞች እንሆናለን። ወይም ዮሐንስ በሌሎቹ ወንጌላት የተጻፉትን ምሳሌዎች አላወቀም ማለት አንችልም። ኢየሱስ በምሳሌዎች በሚያስተምርበት ጊዜ ሁሉ ዮሐንስ ከእርሱ ጋር ነበር። ዮሐንስ እነኝህን ምሳሌዎች ባለመጻፉ ከሌሎቹ የተለየ ያደርገዋል፤ ሆኖም የወንጌሉን ጥቅም አይቀንስም።
2. ተአምራት፡- እያንዳንዱ ወንጌል ተአምራትን ይዟል። የተአምራቱ መብዛትና ማነስ ለአንድ ወንጌል ክብደትን አይሰጠውም ወይም አስፈላጊነቱን አይቀንሰውም። የወንጌላቱ አንድ ዓይነት ያለመሆን ለእኛ አስፈላጊ አይደለም። ምናልባትም ኢየሱስ ያደረጋቸው ተአምራት ብዛት የትኛውም ወንጌላዊ ከጻፈው ሊበልጥ ይችላል።
3. ንግግር፡- በዮሐንስ ወንጌል ውስጥ የተጻፉትን የኢየሱስ ንግግሮች አንዳቸውንም በማርቆስ ወንጌል ውስጥ አናገኝም። ይህ ግን

የእያንዳንዱ ወንጌል ዘገባ የተለያየ ነው፤ ነገር ግን አንዱ ከሌላው ይበልጣል ማለት አይደለም። አራቱም እኩል የሆነ አገልግሎት አላቸው። ከወንጌላውያኑ ማንኛቸውም ቢሆኑ ሁሉንም ነገር ሊነግሩን እንዳልቻሉ እናውቃለን፤ ስለዚህ በጽሑፋቸው ላይ ስሕተት አገኘን ብለን ከመናገር መቆጠብ ያስፈልገናል። አራቱን ወንጌላት በአንድነት እናዋሕዳለን ብለን ጊዜያችንንና ጉልበታችንን ማባከን አያስፈልግም። አንዳንድ ጊዜ አንዱን ታሪክ እንኳን ከሁለት ወይም ከሦስት ወንጌላት ለማሰባሰብና ለማሳካት በቂ መረጃዎች አናገኝም።

## ምዕራፍ 26 - ጥያቄዎች

1. በ170 ዓ.ም. አራቱ ወንጌላትን ለማዋሐድ የሞከረው ማን ነበረ?
2. የጻፈውስ በየትኛው ቋንቋና ለየትኞቹ አብያተ ክርስቲያናት ነበረ?
3. ወንጌል ማለት ምን ማለት ነው?
4. አራቱም ወንጌሎች የሚያስፈልጉን ለምንድን ነው?
5. በዮሐንስ ወንጌል ውስጥ የምሳሌዎች ይዘት እንዴት ነው?
6. በወንጌላት ውስጥ የተአምራት ሁኔታ ምን ይመስላል?
7. ብዙ ንግግሮች ያሉት የትኛው ወንጌል ነው?
8. በርእስ በርእስ ይዘታቸውን ያቀነባበረው ማን ነበረ?
9. የአራቱ ወንጌላት ይዘት የተለያየ መሆኑ ምን ያሳየናል?

መጠንቀቅ አለብን። የእኛ ፍላጎት ኢየሱስ ባስተማረውና ባደረገው ነገር ላይ ብቻ ማተኮር አይደለም። እያንዳንዱን ክፍለ ምንባብ በምናነብበት ጊዜ የሚከተለውን ጥይቄ ራሳችንን መጠየቅ ይኖርብናል። ይህ ያነበብነው ክፍለ ምንባብ የእግዚአብሔር ልጅ የሆነው ኢየሱስ ወደ ዓለም መጥቶ በሰውና በእግዚአብሔር መካከል ሰላምን ስለማምጣቱ እንዴት አድርጎ አቅርቦልናል?

የእያንዳንዱን ወንጌል መጨረሻ ክፍል በምንመለከትበት ጊዜና እያንዳንዳቸው በሕማማቱ ዘገባ ላይ የሚሰጡትን ትኩረት ስናመዛዝን የዘገባውን ትርጉምና ዓላማ ለመረዳት ይረዳናል። ወንጌላቱ የሚሰጡን ዘገባ ወይም መረጃ ብቻ አይደለም፤ ነገር ግን ይህ እንዴት በአንባቢው ሕይወት ውስጥ መሥራት እንደሚገባው ይገልጹልናል። ወንጌላውያኑ ያተኮሩበት ኢየሱስ ምን እንዳደረገ በመግለጹ ላይ ብቻ ሳይሆን አሁንስ ምን ያደርጋል? በሚለው ላይ ነው።

የእያንዳንዱ ወንጌላዊ ጽሑፍ አጀማመር የተለያየ መሆኑን አስተውለናል። ማቴዎስና ሉቃስ ያቀረቡት ዘገባ በመጠኑ ተመሳሳይ ነው። ማርቆስ ስለ ኢየሱስ መወለድ ምንም ያቀረበው ዘገባ የለም። ዮሐንስ ደግሞ የሰው ልጅ ወደ ዓለም ከመምጣቱ በፊት ያለውን በመጠቆም ይጽፋል።

የመጥምቁ ዮሐንስ አገልግሎት ለአራቱም ወንጌላውያን የተለየ ስፍራ ቢኖረውም። አራቱ ወንጌላት ግን የአገልግሎቱን ዘገባ እኩል አልጻፉም። ሆኖም የዮሐንስ ጥምቀት ለኢየሱስ መምጣት መድረክ አዘጋጀ።

ሚልክያስ ከሞተበት ማለትም ከኢየሱስ ልደት ከ400 ዓመታት ወዲህ በይሁዳ ነቢይ አልተነሣም ነበር። በዚህ ምክንያት አይሁዶች በጣም ያዘኑ መሆናቸውን ከአይሁድ የሃይማኖት መጻሕፍት እንረዳለን።

ይኸውም የእግዚአብሔር ልጅ ኢየሱስ አዳኝ ሆኖ እንዴት እንደመጣ ለመግለጽ ነው። አራቱም ወንጌላውያን በወንጌላቸው ውስጥ ለመጥምቁ ዮሐንስ ልዩ ቦታ ሰጥተውታል። እንዲሁም ኢየሱስ በይሁዳ አገር በተለይም በሁለት ስፍራዎች ውስጥ ያደረገውን አራቱም ይነግሩናል። ኢየሱስ ወደ ግብፅ፥ ኤዶም፥ ግሪክ፥ እስያ፥ ሶርያ፥ አረብያ፥ ባቢሎን ወይም ትንሽ ራቅ ወደሚሉ አንዳንድ አገሮች መሄድ ይችል ነበር። ይሁን እንጂ አራቱም ወንጌላት የሚነግሩን ኢየሱስ በገሊላና በይሁዳ ያደረገውን ብቻ ነው።

ማቴዎስ ማርቆስና ሉቃስ ኢየሱስ በገሊላ የሰጠውን አገልግሎት በብዛት እንደሚነግሩንና የኢየሩሳሌምንም አገልግሎት በጨረፍታ እንደሚያልፉት ቀደም ብለን ተመልክተናል። ዮሐንስ ስለ ኢየሩሳሌም አገልግሎት በብዛት ይተርክልናል። ሆኖም የገሊላንም አገልግሎት ችላ አላለም። ወንጌላውያን በሙሉ ከኢየሱስ ጋር የቆዩ ወይም ከኢየሱስ ጋር ከነበሩት ሐዋርያት ጋር የቅርብ ግንኙነት የነበራቸው ሰዎች ነበሩ። ኢየሱስ በዚያን ወቅት ላደረገው ነገር እንግዳ አልነበሩም።

ኢየሱስ በሦስት ዓመት ውስጥ ያደረገውን በሙሉ ለመግለጽ ማንኛቸውም አልሞከሩም። ለዘገባቸው የሚያስፈልጋቸውን እንዲመርጡ መንፈስ ቅዱስ እያንዳንዳቸውን መራቸው።

ኢየሱስ በኢያሪኮ የፈጸመው ታሪክ ከዚህ ቀጥሎ ባሉት ጥቅሶች ውስጥ ያገኛል (ማቴ. 20፡29-34፤ ማር. 10፡46-52፤ ሉቃስ 18፡35-43)። የማርቆስን ታሪክ በአንድ ደብተር ላይ ሁለት መሥመር ከላይ ሁለት መሥመር ከታች እየዘለላችሁ ገልብጡት። ቀጥላችሁ ደግሞ ከላይ በዘለላችሁት የላይኛው መሥመር ላይ ማቴዎስ የጨመራቸውን ቃላት ጻፉ። በታችኛው መስመር ደግሞ ሉቃስ የጨመራቸውን ቃላት ጻፉ። እንዲህ ካደረጋችሁ በኋላ በታሪኩ ውስጥ ጥቂት ልዩነቶችን

የተደረገ ሙከራ የለም። እነዚህ ልዩነቶች የቀደሙትን አንባቢያን አላስጨነቋቸውም። የልዩነታቸውን አመጣጥ እርግጠኛ ሁኔታ ብናውቅ ምናልባት ልዩነቱ ሊጠፉ ይችል ነበር። ኢየሱስ ምን እንዳደረገና ለምን እንዳደረገው በወንጌላቱ ሁሉ ውስጥ ግልጽ ነው። አስፈላጊዎቹም እነዚሁ ናቸው።

## ምዕራፍ ሃያ ሰባት - ጥያቄዎች

1. ዮሐንስ 20፡31 ምን ያሳየናል?
2. ዘገባዎች ሁሉ መልስ የሚሰጡት ለየትኛው ጥያቄ ነው?
3. የሕማማቱ ዘገባ ምን ያሳየናል?
4. ማቴዎስና ሉቃስ የሚጀምሩት በምንድን ነው?
5. ማርቆስ የሚጀምረው በምንድን ነው?
6. ዮሐንስ ወንጌሉን የጀመረው እንዴት ነው?
7. በእያንዳንዱ ወንጌል መክፈቻ ላይ ልዩ ትኩረት የተሰጠው የትኛው ድርጊት ነው?
8. ወንጌላውያኑ የሚናገሩት ስለ የትኞቹ አውራጃዎች ነው?
9. አብዝቶ ስለ ኢየሩሳሌም የሚነግረን ማን ነው?
10. በማቴ.20፡29-34 ላይ የምናገኘው ታሪክ ምን ያሳየናል?
11. ጥንታዊ ክርስቲያኖች ስለዚህ ልዩነት ምን አደረጉ?

እናገኛለን። በአእምሮአችን አጠቃላይ የሆነ ምስል ለማስቀመጥ ጥረት ካላደረግን በስተቀር አራቱ ወንጌላት የያዙት ልዩነቶች ግራ ሊያጋቡን ይችላል።

ይህንን ለማድረግ የወንጌሎችን ይዘት በአሥራ አንድ ክፍሎች መከፈልና እያንዳንዱ ክፍል ከወንጌላቱ በየትኛው ስፍራ እንደሚገኝ ቀስ በቀስ ማጥናት ይኖርብናል። ቀደም ብለን እያንዳንዱን በተናጠል ተመልክተናል። አሁን ደግሞ በአጠቃላይ እንመለከታቸዋለን። ክፍሎቹን ከ1-11 ብለን እንሰይማቸውና እያንዳንዱ ክፍል በየትኛው ወንጌል እንደሚገኝ እንመለከታለን።

1. መግቢያ፤ ሉቃስና ዮሐንስ ብቻ መግቢያ አላቸው። የሉቃስ መግቢያ በጣም አጭር ነው (ሉቃስ 1፡ 1-5)። ዮሐንስ 18 ጥቅሶች ይሰጠናል (ዮሐንስ 1፡ 1-18)።

2. ልደቱ፤ ሉቃስና ማቴዎስ ያቀረቡት ታሪኮች ተመሳሳይ አይደሉም፤ ሆኖም ሁለቱም ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ልደት ሁለት ሁለት ምዕራፍ ሰጥተውታል።

3. መቅድም፤ መቅድም ስንል የመጥምቁ ዮሐንስን ሥራ ማለታችን ነው። ይህንን በአራቱም ወንጌላት ውስጥ እናገኛለን። እያንዳንዱ ወንጌላዊ ታሪኩን በተለያየ መንገድ ያቀርበዋል። አሳቡ ግን አንድ ዓይነት ነው።

4. ገሊላ፤ ማቴዎስ፥ ማርቆስና ሉቃስ በዝርዝር አቅርበዋል። ዮሐንስም ኢየሱስ በገሊላ የሠራውን ይነግረናል፤ ግን ከሌሎቹ ለየት ባለ መንገድ ነው። የእርሱ ዘገባ ኢየሱስ በኢየሩሳሌም ከነበረው አገልግሎት ጋር የተያያዘው ነው።

የተፈጸመ ድርጊት ሲሆን በሉቃስ ምዕራፍ 9-11 ውስጥ ይገኛል። ይህንን ስናስታውስ ተመሣሣይ ድርጊት በሌሎቹ ወንጌላት ውስጥ ተፈጽሞአል ብለን መፈለግ የለብንም።

7. መግባት፤ በአራቱም ወንጌላት ውስጥ ይገኛል። ይህ ኢየሱስ ለመጨረሻ ጊዜ ወደ ኢየሩሳሌም ሲገባ ነው። አራቱም ወንጌላት ይህንን ታሪክ በተመሳሳይ መንገድ ይነግሩናል። ይህ ክፍል ኢየሱስ በመጨረሻው ሳምንት በኢየሩሳሌም ውስጥ የፈጸማቸውን ድርጊቶች ያጠቃልላል።

8. መመሪያ፤ ይህ የዮሐንስ ልዩ አስተዋጽኦ ነው። መመሪያውም ኢየሱስ ለደቀ መዛሙርቱ የሰጠው ትምህርት ሲሆን በዮሐንስ 13-17 ባለው ውስጥ ይገኛል።

9. የሕማማቱ ዘገባ፤ በአራቱም ወንጌላት ይገኛሉ። ይህ ክፍል በመጨረሻዎቹ ቀናት በኢየሩሳሌም የተፈጸሙትን ሁኔታዎች ያጠቃልላል። ይህንን በዚህ ጥናት በ14ኛው ምዕራፍ ውስጥ እንደተመለከትነው ከወንጌላቱ ውስጥ ቀድሞ የተጻፈው ይህ የሕማማቱ ዘገባ ነው። በዚህ ላይ አራቱም ወንጌላት በጣም ተመሳሳይነት እንዳላቸውም ተመልክተናል።

10. ትንሣኤ፤ አራቱም ወንጌላት አስፍረውታል። ከዮሐንስ ወንጌል በስተቀር ለሌሎቹ ይህ የመጨረሻው ምዕራፋቸው ነው።

11. መደምደሚያ፤ ዮሐንስ በምዕራፍ 21 ውስጥ ያሠፈረው ዘገባ ኢየሱስ ከትንሣኤ በኋላ የሠራውን ጨምሮ አብራርቷል።

አራቱ ወንጌላት እንዴት አብረው ሊሄዱ እንደሚችሉ በቅድሚያ ለመረዳት የእነኝህን ጽሑፍ ክፍሎች በቃላችሁ አጥኑ።

ምንም ግራ ሳንጋባ በአእምሮአችን ከማቴዎስና ከዮሐንስ ጋር ሳናደባልቀው ማርቆስ የሚያቀርበውን ልዩ አስተዋጽኦ በሚገባ ልንረዳ እንችላለን። ጠቅላላውን የወንጌላት ይዘት ስንረዳ፥ ማለትም በአንድ ጊዜ አራቱንም ወንጌላት ማስተዋል ስንችል ብዙ ጥቅም እናገኝበታለን።

በመጨረሻም አራቱ ወንጌላት በአንድነት የሚስማሙባቸውን አራት ዋና ዋና ነጥቦች አስተውሉ። እነኝህም:- የመጥምቁ ዮሐንስ አገልግሎት፥ የኢየሱስ ወደ ኢየሩሳሌም መግባት፥ የሕማማቱ ዘገባና የትንሣኤው ዘገባ ናቸው።

### ምዕራፍ ሃያ ስምንት - ጥያቄዎች

1. የወንጌላትን ይዘት መረዳት የምንችለው እንዴት ነው?
2. የአራቱን ወንጌላት አጠቃላይ ይዘት በስንት ዋና ዋና ክፍሎች ልንከፋፍለው እንችላለን?
3. ወንጌላውያን ሁሉ የሚስማሙት በየትኞቹ አራት ዋና ዋና ነጥቦች ላይ ነው?

# ምዕራፍ 29

## ወንጌላት የተጻፉት መቼ ነው?

ኢየሱስ የተሰቀለው በ33 ዓመተ ምሕረት ነበረ ብንል ከእውነት አልራቅንም። በሐዋርያት ሥራ 18፡21 ውስጥ ባገኘነው ማስረጃ መሠረት ጳውሎስ ከ51-52 ዓ.ም. ውስጥ በቆሮንቶስ እንደነበረ እናውቃለን። ይህም የሚያመለክተን የሐዋርያት ሥራ 1-18 ያለው ክፍል የተፈጸመው ከ33-56 ዓመተ ምሕረት ድረስ መሆኑን ነው። አሁን የምንነጋገረው ሁኔታው ተፈጽሞ ካለፈ ከብዙ ምእተ ዓመታት በኋላ ለውጦችን ስላመጣ ነገር አለመሆኑን መረዳት አለብን።

[illegible] ያውቁ በነበረበት በቁራ በአገሪቱ [illegible] በቋንቋ ውስጥ ነበር።

የወንጌላቱን አጻጻፍ በሚመለከት ረገድ የአፈ ታሪኮችን አገልግሎት ማንሣት ትክክል ላይሆን ይችላል። አይሁዶች በዚያን ወቅት ማንበብና መጻፍን የሚያውቁ የተማሩ ሕዝቦች መሆናቸውን እናውቃለን። እግዚአብሔር የተናገረውንና የሠራውን ሥራ የመጻፍ ባሕላቸው ቢያንስ ቢያንስ ከሙሴ ዘመን ጀምሮ መሆኑንም እናውቃለን። ከዚህም ሌላ ብዙ መቶ ዓመት ከሙሴ በፊት በባቢሎን ያሉ ሰዎች መጻፍ ይችሉ ስለነበረ አብርሃም እግዚአብሔር ያደረገለትንና የተናገረውን በጽሑፍ አስተላልፎ ሊሆን ይችላል።

አዲስ ኪዳንን ያመነጨችው ቤተ ክርስቲያን ነች። ስለዚህ ቤተ ክርስቲያን ከመጽሐፍ ቅዱስ ይልቅ አስፈላጊ ነች የሚሉ አንዳንድ ሰዎች አሉ። ይህ ግን በጭራሽ የተሣሣተ አመለካከት ነው። የኢየሱስ ታሪክ ከመጻፉ በፊት ለብዙ ትውልድ አባቶቹ ለልጆቻቸው በቃላቸው ያስተላለፉትን ታሪኮች አይደለም። የትኞቹ ታሪኮች፤ ምሳሌዎችና ተአምራት በየትኛው ወንጌል ውስጥ መግባት እንዳለባቸው የትኛውም የቤተ ክርስቲያን ጉባዔ ተሰብስቦ አልወሰነም። የኢየሱስ ተከታይ የነበሩት በተለይም ምሁር የነበረው ማቴዎስ ኢየሱስ ያደረገውንና የሠራውን ወዲያውኑ ይጽፍ ነበር። ይሁን እንጂ 12ቱ ሐዋርያት በሕይወት እስከነበሩ ድረስ ሥልጣን የተሰጠው ጽሑፍ የመኖሩ አስፈላጊነት አልነበረም። ታሪኩን በትክክል እንዲያስተላልፉ ኢየሱስ የመረጣቸው እነርሱን ነበርና። ከ70 ዓ.ም. በፊት ከያዕቆብ በስተቀር ከእነርሱ ውስጥ የሞተ ሰው ለመኖሩ ምንም ማስረጃ የለንም (የሐዋ. 12)። ብዙዎቹ የጳውሎስ መልእክቶች የተጻፉት ከ40-60 ዓ.ም. ለመሆኑ ምንም አያጠራጥርም። አብያተ ክርስቲያናት እነዚህን መልእክቶች ያሰባሰቧቸው መቼ እንደሆነ ግን አናውቅም። ጴጥሮስ ሁለተኛ መልእክቱን በጻፈበት ጊዜ አንዳንዶቹ የጳውሎስ መልእክቶች መለኮታዊ ሥልጣን

የሉቃስን ወንጌል መጀመሪያ ረቂቅ ሊሆን ይችላል።

ማቴዎስ፥ ማርቆስና ሉቃስ ኢየሱስ ስለ መጨረሻው ዘመን ያስተማረውን በዝርዝር ማቅረባቸውን ቀደም ብለን ተመልክተናል። አንዱ የሌለኛውን የሚያመለክት በመሆኑ ይህ ትምህርት በ70 ዓ.ም. ከተፈጸመው የኢየሩሳሌም መደምሰስ ጋር የተያያዘ ነው። ከእነኚህ ጽሑፎች አንዳቸውም ከከተማይቱ መደምሰስ በኋላ ያለመጻፋቸው ግልጽ ይመስላል። ማቴዎስ፥ ማርቆስና ሉቃስ ከከተማይቱ መደምሰስ በኋላ ወንጌላቸውን ጽፈው የከተማይቱን መደምሰስ ሳይጠቅሱ ያልፉሉ ወይም ይዘሉታል ብሎ ማመን በጣም አስቸጋሪ ነው።

ስለሆነም አራቱም ወንጌላት ከ70 ዓ.ም. በፊት ማለትም የመዘገቡአቸው ድርጊቶች ከተፈጸሙ 40 ዓመት ሳያልፍ ተጽፈው ነበር ብለን ለመናገር እንደፍራለን። ታሪኩ ትክክል ባይሆን ኖሮ በዓለም ዙሪያ በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ ሰዎች ታሪኩን በካዱ ነበር። ለምሳሌ አይሁዶች ክርስቲያኖችን ለብሉይ ኪዳን የተሳሳተ ትርጉም ይሰጣሉ ብለው አጉረመረሙ እንጂ የወንጌልን ታሪክ ለመካድ አንድም ተጨባጭ ማስረጃ ማቅረብ አልቻሉም።

### ምዕራፍ ሃያ ዘጠኝ - ጥያቄዎች

1. የሐዋ.18፡12 ምን ያሳየናል?
2. በሐዋ.1-18 የተመዘገቡት ድርጊቶች የተፈጸሙት መቼ ነው?
3. ጥንታዊ ክርስቲያኖች መስበክ የጀመሩት የት ነው?
4. የአይሁዶች የትምህርት ይዘት እንዴት ነበረ?
5. የክርስቲያኖችን ወግ የሚቆጣጠሩት እነማን ነበሩ?
6. የጳውሎስ መልእክቶች የተጻፉት መቼ ነው?

# ምዕራፍ 30

## መለኮታዊ ትምህርትና ታሪክ

የአራቱ ወንጌላውያን ጽሑፍ የኢየሱስ የሕይወት ታሪክ እንዲሆን ታቅዶ የተጻፈ አለመሆኑን ተምረናል። የጸሐፊዎቹ ዓላማ ይህ አለመሆኑን በግልጽ ተረድተን ሥራቸውን ባላሰቡት መንገድ እንዳንተረጉም መጠንቀቅ ይኖርብናል።

ጳውሎስ በገላትያ 1፡6-8 እንዳመለከተው ወንጌል አንድ ብቻ ነው። እንደዚህ ማለት ምን ማለቱ ነው? ኢየሱስ ወደ ዓለም ስለመምጣቱ ብዙ የተለያዩ ትርጉሞች የሉንም። ብዙ የተለያዩ ነገሮችን አድርጎአል፥ ሆኖም ያደረገው ነገር ሁሉ ያለው ዓላማ አንድ ብቻ ነው። አራቱ ወንጌላውያንም የጻፉት ይህንኑ በሚመለከት ነው።

ስለ አራቱ ወንጌላት ስንናገር ግራ ሊያጋባን ይችላል። ይህንን ቃል ስንጠቀም አራት ገጽታዎች ስላሉት ስለ አንዱ ወንጌል መናገራችንን ማስተዋል አለብን። ይህም ማለት አራት ማዕዘናት ያሉትን ዓለት ከላይ ወደ ታች እንደመመልከት ነው። እያንዳንዱ ማዕዘን ለየት ያለ ቢመስልም የዚያው የአንዱ ዓለት አካል ነው። የአራቱ ወንጌላውያን ዘገባም ይህንን ይመስላል።

አራቱ ወንጌላውያን ኢየሱስ ያስተማረውንና የሠራውን ሥራ በመሰብሰብ በታሪክ መልክ ለማስፈር የተነሣሱ ጸሐፊዎች አልነበሩም። የጻፉት ነገር ለሚሰጠው ትርጉም የማይጨነቁ ሰዎችም አልነበሩም። አራቱ ወንጌላውያን ያቀረቡት ጽሑፍ ልዩ የሆነ ትኩረት ነበረው። ለዚህም ሦስት ምክንያቶች አሉት፡-

1. የተፈጸሙት ድርጊቶች ሁሉ ከብሉይ ኪዳን ጋር የተዛመዱ ናቸው። በየትም ቦታ ያሉ አይሁዶች ብሉይ ኪዳንን እንደ እግዚአብሔር ቃል

3. ከኢየሱስ ጋር ከነበራቸው ግንኙነት የተነሳ የወንጌላውያኑ ሕይወት ተለውጦ ነበር። ስለሆነም የጻፉት እንደተመልካች ሳይሆን በራሳቸው ሕይወት እንደተፈጸመ፥ እንደ ተለማመዱትና እንደሚያውቁት ነው።

አራቱ ወንጌላውያን በተለያዩ ወቅቶች የተፈጸሙትን ድርጊቶች አጣምረው ከውስጡ የሆነ ዓይነት ትርጉም ለማውጣት አልሞከሩም። መተርጎምም አላስፈለጋቸውም። የኢየሱስን ወደ ዓለም የመምጣት ሐቅ እንዳለ ግልጽ አደረጉልን። አንድ ሁኔታን እንደ ምሳሌ አድርገን እንውሰድ (ሉቃስ 2፡ 1-7)።

ይህ ታሪካዊ ሐቅ ነው ብለን እንቆጥረዋለን። ሰዎች ሁሉ እንዲመዘገቡ አውጉስጦስ ቄሳር የተባለው የሮም አስተዳዳሪ ትእዛዝ አወጣ። ይህ ትእዛዝ የተሰጠበት ጊዜ መቼ እንደነበረ እናውቃለን። ማርያምና ዮሴፍ ከገሊላ ወደ ይሁዳ ቤተልሔም መሄዳቸውን እናውቃለን። ማርያም በቤተልሔም ልጇን መውለዷን እናውቃለን።

ከላይ በተጠቀሱት ሦስት ምክንያቶች ማለትም ብሉይ ኪዳን፥ የኢየሱስ ማንነትና ያለውን የመለወጥ ኃይል የሚያሳየው ታሪካዊ ማብራሪያ የታሪኩ መጨረሻ አይሆንም። እነኝህ ሦስት ነጥቦች በታሪካዊነታቸው ለሉቃስ 2፡1-7 ተወዳዳሪ የማይገኝለት ክብደት ይሰጡታል።

ስለሆነም አራቱንም ወንጌላውያን የመለኮት ትምህርት መምህራንና የታሪክ ምሁራን ናቸው ብለን ብንጠራቸው ትክክለኞች ነን። ለምን? የታሪክን ሐቅ በትክክል ይነግሩናል። እንዲሁም የእነዚህ ሐቆች ትርጉም በሚቀበላቸው ሰው ሕይወት ውስጥ ምን ዓይነት ለውጥ እንደሚያመጣ ይነግሩናል።

የእግዚአብሔር መገለጥ ጋር የተያያዘው እንዴት ነው? እግዚአብሔር ቀደም ብሎ ስለራሱ በነገረን ላይ ሌላ ምን ተጨማሪ ነገር አለው?

2. ከኢየሱስ አገልግሎት ጋር እንዴት ይዛመዳል? ስለ ኢየሱስ ምን ተጨማሪ አሳብ ይሰጠናል?

3. በአሁኑ ጊዜ ሕይወቴን በምን መንገድ ይለውጠዋል? ይህ ስለ ሆነስ ምን ማድረግ አለብኝ? እንዴትስ መኖር ይገባኛል?

### ምዕራፍ ሠላሳ - ጥያቄዎች

1. የወንጌላውያን ዓላማ ምን ነበረ?

2. ገላ.1፡6-8 ምን ያሳያል?

3. ታድያ እንዴት አራት ወንጌሎች አሉ ማለት እንችላለን?

4. በወንጌላት ውስጥ የተመዘገቡት ነገሮች ልዩ ጥቅም ያላቸው ለምንድን ነው?

5. ለእነዚህ ድርጊቶች ዓይነተኛ ትርጉም የሰጠው ማን ነበር?

6. ወንጌላውያንን እንዴት ታሪካዊ ጸሐፊዎችና የመለኮት ትምህርት አቅራቢዎች ልንላቸው እንችላለን?

# ምዕራፍ 31

## ወንጌል ምንድን ነው?

መልአኩ የሕፃኑን ስም ለወላጆቹ በነገረ ጊዜ ወንጌልን ያበሠረው፡- ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ ዓለም የመጣው ሰውን ለማዳን ነው በማለት ነበር። ወንጌል ማለት ይኸው ነው። ኢየሱስ ወደ ዓለም የመጣበት ምክንያት ይኸው ነው። የኢየሱስ ሥራ ይኸው ነው። የአራቱን ወንጌላውያን መጻሕፍት በምናነብበት ጊዜ ራሳችንን እንጠይቅ፡- እንዴት ነው የሚያድነው? ማንን ነው የሚያድነው? መቼ ነው የሚያድነው? ወ.ዘ.ተ.

በማንኛውም ጊዜና ሁኔታ የእርሱ የማዳን ኃይል ሊረዳን ዝግጁ ነው። ሕያው ሆኖ ስለሚኖር በማንኛውም ጊዜ ሊረዳን ይችላል። ወንጌል ይህ ነው።

የወንጌል ምንጭ ወይም መነሻ ምንድን ነው? የወንጌል ምንጭ ኢየሱስ ራሱ ነው። የቤተ ክርስቲያን ወይም የሐዋርያት የልምምድ ውጤት አይደለም። ወንጌል ራሱ በራሱ ሥልጣኑን ያሳውቃል ማለት ነው። ወንጌልን እንደተላለፈልን ሳንጨምር ሳንቀንስ ወይም ሳናርመው እንዳለ ሲደርሰን ሙሉ ለሙሉ እውነት ሆኖ ነው ያገኘነው። በውስጡ ስሕተት ወይም ድክመት የለበትም። መለወጥ ወይም መሻሻል አያሻውም።

መምህራን በክርስቲያኖች ላይ ድክመትን ስላዩ የተለያዩ ትምህርቶችን አጋነው አስተምረዋል። ክርስቲያኖች እንኳ ይህን ሲመለከቱ እነዚህ መምህራን የማይስማሙበትን ትምህርቶች ብቻ አጉልተው ያስተማሩ ይመስላቸዋል። ሆኖም ክርስቲያኖች በሙሉ ወንጌል ምን እንደሆነ፥ ምን ትርጉም እንዳለው ካስተዋሉና ያንንም አጉልተው ካስተማሩ እውነተኛው የክርስቲያኖች አንድነት ይፈጠራል።

የተቀበልናቸው አራቱም ወንጌላት በዓይን ምስክሮች መጻፋቸውን እርግጠኞች ነን። ታሪኩ ከተፈጸመ ከብዙ ዘመናት በኋላ የተጻፉ አይደሉም። እነኝህ ሰዎች ለኢየሱስ በጣም ቅርብ የሆኑ ናቸው። ሦስት ዓመት ከእርሱ ጋር የተጓዙ ናቸው፥ የሠራውን ሥራ በቅርብ ሆነው ተከታትለዋል፥ ሲያስተምርም አዳምጠዋል። ጽሑፋቸውንም ያዘጋጁት ስለሁኔታው ለሚያውቁ ሰዎች ነበር። የጻፉትን ታሪክ ዋና ዋና ነጥቦች የሚገመግሙ በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ ሰዎች ነበሩ። ወንጌላውያኑ ሁሉ በጽሑፋቸው ላቀረቡት ሁኔታ የዓይን ምስክሮች ነበሩ ለማለት እንደፍራለን።

ወንጌላውያኑ እግዚአብሔር እንዲጽፉ የፈለገውን ብቻ ጽፈዋል ማለታችን ነው። ይህንንም ስንል እያንዳንዱን የወንጌል ክፍል ለመረዳት እንደማያስቸግረን ለመግለጽ መሞከራችን አይደለም። ወይም የመጀመሪያው ብራናዎች በጸሐፊዎች ሲገለበጡ ወይም ሲታተሙ ሰዎች የሚፈጥሩት የፊደል ስሕተት አይገኝባቸውም ማለታችን አይደለም። ይህ የመጀመሪያዎቹ ጸሐፊዎች ስህተት ሳይሆን ከእነርሱ በኋላ የሠሩት ሰዎች ስሕተት ነው። የመጀመሪያዎቹ ጽሑፎች ፍጹማን ናቸው ማለት ስሕተት የማይገኝባቸው ናቸው ማለታችን ነው።

ስለዚህ ወንጌል ታሪክ ነው። ወንጌል ኢየሱስ ማን መሆኑን፥ ምን እንዳስተማረና ምን እንዳደረገ የሚገልጽ ጽሑፍ ነው። ወንጌል ራሳቸው ከጌታ ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር በሚተባበሩ ሰዎች ሕይወት ውስጥ የሚሠራ ኃይል ነው። ይህ ኃይል የማይታወቅ ወይም ለመግለጽ የማይቻል አይደለም። በወንጌላውያኑ ጽሑፍ ላይ የተመሠረተ ነው።

ወንጌል የሚሰበክና በተግባር የሚተረጎም ነው። ኢየሱስ ማን መሆኑን ምን እንደሠራና ምን እንዳስተማረ ለሰው ዘር በሙሉ እንድንነግር ታዘናል። የምንሰብከውም ሐቅ እውነት መሆኑን በምንኖረው ሕይወት ማሳየት አለብን። ኢየሱስ ከሞት መነሣቱን ሐዋርያት መስክረዋል። ኢየሱስ ዛሬም ሕያው መሆኑንና ኃይሉም እንደ ጥንቱ አሁንም መሥራቱን እንድንመሰክር ተጠርተናል።

## ምዕራፍ ሠላሳ አንድ - ጥያቄዎች

1. ደኅንነት ማለት ምን ማለት ነው?

2. ወንጌል የመንጪው ከማን ነው?

3. እውነተኛ አንድነት የሚገለጸው መቼ ነው?

4. እነዚህን ድርጊቶች ሁሉ የመዘገቡት ሰዎች እነማን ነበሩ?

7. ወንጌላውያን ስለጻፉት ጽሑፍ ምን ማለት እንችላለን?

8. የወንጌል ሥልጣን መሠረት ምንድን ነው?

2. ዮሐንስ የጻፈው ዘገባ የኢየሱስን የሕይወት ታሪክ ብቻ ለማቅረብ አለማሰቡን ያሳየናል።

3. ያቀረበው ማብራሪያ አስፈላጊ አልነበረም።

4. በማቴዎስና በሉቃስ

5. የትውልድ ሐረግ ዝርዝር፥ ልደቱ፥ የአሕዛብ ጠቢባን ጥየቃና ወደ ግብፅ መሸሹ ነው።

6. የኢየሱስን አገልግሎት ከብሉይ ኪዳን ጋር ለማያያዝ ነው።

7. ሉቃስ ወንጌሉን እንዴት አድርጎ እንዳቀነባበረ ይገልጻል።

8. ሁለቱ ነጥቦች የኢየሱስንና የመጥምቁ ዮሐንስ አገልግሎት እንዴት እንደ ተያያዙ የሚያሳዩ ናቸው።

9. የኢየሱስ ወደ ዓለም መምጣት ፈጽሞ አዲስና ልዩ ትርጉም ያዘለ ድርጊት መሆኑ ነው።

## ምዕራፍ ሁለት - መልሶች

1. ሉቃስ።

2. አገልግሎቱ ከብሉይ ኪዳን ጋር መያያዙ፥ አገልግሎቱና ሞቱ።

3. የ30 ዓመት ነበር።

4. ሉቃስ።

5. ማርቆስና ዮሐንስ ናቸው።

6. የ17 1/2 ዓመት ነበር።

7. ለአይሁድ ሁሉ ምልክት መሆን ነበር።

8. ሚልክያስ 4 ውስጥ ነው።

9. በእነዚያ ዓመት ውስጥ ኢየሱስ አላገለገለም።

3. ኢየሱስ ወደ ኢየሩሳሌም ለመሄድ አሳቡን ቆርጦ እንደተነሣ ያሳያል።

4. አሥር ከተማዎች፥ ገሊላ፥ ሰማርያ፥ ፊርያና ይሁዳ ናቸው።

5. በገሊላ ባሕር፥ በሰማርያና በኢየሩሳሌም አካባቢ ነበር።

6. ወደ ደቡብ ለመሄድ እንደተነሣ ነው።

7. ኢየሱስ ገሊላን ለቅቆ ወደ ይሁዳ እንደወጣ።

8. ከኢየሩሳሌምና ከቤተ መቅደሱ ተገልሎ ነበር።

9. የገሊላ ሰዎች ትምህርቱን ለመቀበልና ሥራውን ለማስተዋል ፈቃደኞች ስለ ነበሩ።

## ምዕራፍ አራት - መልሶች

1. የእግዚአብሔር ዕቅድ መቤዠት እንደሆነ ያመለክታል።

2. ኢየሩሳሌም ነበር።

3. በዘፍጥረት 14 ላይ ነው።

4. በምዕ. 21-28 ውስጥ ነው።

5. 37% ያህሉ ይገልጻል።

6. ስድስት ምዕራፎች ሰጥቷል እነርሱም 19-24

7. ዮሐንስ ስለ ይሁዳ አገልግሎት ሰፋ ያለ ዘገባ ይሰጣል።

8. ከ33 ዓመት የአገልግሎት ዘመን ውስጥ አንድ ሳምንት ብቻ በኢየሩሳሌም አገለገለ።

## ምዕራፍ አምስት - መልሶች

1. በማቴ.26-27፤ ማር.14-15፤ ሉቃስ 22-23ና ዮሐ.18-19 ውስጥ ይገኛል።

2. የትንሣኤ ዘገባ ብለን ሰይመነዋል።

7. ልዩ ባሕርያት የሏቸውም።

8. ጸሐፊዎች ሁሉ በሞቱ ላይ ትኩረት እንደሰጡ ያሳየናል።

9. አንዱ ለሌላው ሊሞት እንደሚችል ያሳያል።

## ምዕራፍ ስድስት - መልሶች

1. ማብራሪያ ወይም መልእክት ማለት ነው።

2. ሐዋርያት ለአብያተ ክርስቲያናት ያስተላለፉት ትምህርት ማለት ነው።

3. የክርስቲያኖችን ትምህርት መቆጣጠር ነበር።

4. በሐዋርያት ሥልጣን ላይ ነው።

5. ሥልጣን ያለው መልእክተኛ ማለት ነው።

6. ከቤተ ክርስቲያን የተላኩ መልእክተኞች ነበሩ።

7. የቤተ ክርስቲያን ሥልጣን ተገልጧል።

8. የፊልጵስዩስ ቤተ ክርስቲያን ምስክርነት ነው

9. ኢየሱስ - ሐዋርያት - ጽሑፎች - ቤተ ክርስቲያን

## ምዕራፍ ሰባት - መልሶች

1. በሮም መንግሥት አስተዳደር ሶርያ በተባለው ክፍለ አገር ውስጥ ነበረች።

2. በኢየሩሳሌም ነበር።

3. ከሶርያዋ አንጾኪያና ከፊልጵስዩስ ጋር ነው።

4. ከሐዋ. 13-14 ናቸው።

5. ፊልጵስዩስ ትባል ነበር።

6. ከአይሁድ ወገን ላመኑት ክርስቲያኖች ነው።

10. በኤፌሶን ሊሆን ይችላል።

11. በአራት ቡድኖች:- ምዕራባዊ፥ ግሪካዊ፥ አይሁዳዊና ግብጻዊ።

12. ተመሳሳይ ብራናዎች ነው።

## ምዕራፍ ስምንት - መልሶች

1. ደኅንነት።

2. የምትሰብከውን ወንጌል መከላከል አስፈለጋት።

3. ለአይሁዶች ነው።

4. ወንጌሉ ፍጹም አዲስ ሳይሆን ከብሉይ ኪዳን ጋር መዛመዱን ያሳያል።

5. የመሢሑን መምጣት ነው።

6. ከሮም መንግሥት ያድነናል ብለው ተስፋ አድርገው ነበር።

7. የናዝሬቱ ኢየሱስ ያ የተጠበቀው መሢህ መሆኑን ከብሉይ ኪዳን በመጥቀስ ማስረዳት ያስፈልጋቸው ነበር።

8. ክርስቲያኖች ስለ ብሉይ ኪዳን የነበራቸውን አመለካከት ያስረዱናል።

## ምዕራፍ ዘጠኝ - መልሶች

1. በግልጽ ዓላማ የተያያዙና አንድ ታሪክ የያዙ እንደሆነ ነው።

2. ራሱን እንደቻለ የስብከት ንድፍ ልንመለከተው እንችላለን።

3. ለክርስቲያኖች ትምህርት የመሆን አገልግሎት ነበራቸው።

4. አምስት ይገኛሉ።

5. 2 ዓይነት ሲሆኑ እነርሱም ስብከትና ትምህርት ናቸው።

6. ከኢየሱስ በተሰጠው መልእክት ላይ ነበር።

7. ማኅበረሰብ የራሱ የሆነው ታሪክ ስለሚፈጥር ነው።

8. ለእግዚአብሔር ቃል ነው።

3. አራምኛ ነበረ።

4. ተረስቶ ነበረ።

5. የግሪክ ቋንቋ ነበረ።

6. የግሪክ መንግሥት በሥልጣን ላይ በነበረበት ጊዜ ቋንቋቸውና ባሕላቸው በየቦታው ተቀባይነት በማግኘቱ ነበር።

7. ታሪኩ ብዙ ገጽታዎች ስላሉትና አንድ ጽሑፍም ሊያጠቃልለው ስለማይችል ነው።

8. ጸሐፊዎቹ የዘመኑ ሰዎች ከመሆናቸውም በላይ ለዘመናቸው የጻፉት ስለነበር ነው።

9. መንፈስ ቅዱስ መራቸው።

10. አፅምን፥ ካርታን ወይም የቅያሴ ምልክቶችን ይመስላሉ፤ ለታሪኩ የማይለወጥና ሥልጣን ያለው ቅርጽ ይሰጡታል።

## ምዕራፍ አሥራ አንድ - መልሶች

1. በዕብራይስጥ።

2. ሴፕቱዋጀንት በላቲን ቁጥሮች - ሰባ ማለት ነው።

3. ግሪክ

4. ምሁራን ብቻ።

5. አብዛኞቹ ሰዎች ማንበብና መጻፍ ይችሉ ነበር።

6. በቃል ደረጃ ብቻ የተላለፈው መልእክት።

7. ማንበብ ቢችሉም ወንጌል የብሉይ ኪዳን ፍጻሜ ነው።

2. የብሉይ ኪዳን ሥልጣን የማይሻርና የማይለወጥ መሆኑ ነው።

3. የሕይወት መንገድ በብሉይ ኪዳን የተገለጠ መሆኑን ለማሳየት ነው።

4. አዲሱ መልእክት በአዲስ ኪዳን ላይ የተመሠረተ ስለሆነ ነው።

5. አንዱ አዲስ፤ ሌለኛው ያረጀ እንደሆነ።

6. አንዱ ተግባር ሌላውን እንዳሚላው።

7. እግዚአብሔር የሁሉ ገዢ መሆኑ።

8. በአሁኑ ዘመን ስለሚገኘው የክርስቶስ መንግሥት።

9. ከመና መስጠት ታሪክ ጋር ስለ ተዛመደ ነው።

## ምዕራፍ አሥራ ሦስት - መልሶች

1. በተግባር በተለይም በፍጥረት።

2. የተገለጠና የሚታይ ኃይል።

3. ከእነርሱ ጋር ቃል ኪዳን ያደረገውን የሚጠቁም ቃል ነበር።

4. በፍጹም ማወቅ አንችልም ነበር።

5. በመንፈስ ቅዱስ ግፊት የመጻፍ አስፈላጊነትን እወቁ።

6. ሰጪ እግዚአብሔር መሆኑንና ጸሐፊው በፈቃደኝነት መጻፉን።

7. ጸሐፊዎቹን መምራት።

8. መንፈስ ቅዱስ የመራቸው መሆኑን።

## ምዕራፍ አሥራ አራት - መልሶች

1. ከሌሎች ጽሑፎች እየቀዳና እያስተያየ ነው።

2. ጥቅሶችን የሚያብራሩትን ታሪኮች።

7. የሕማማቱ ዘገባ በ56 ዓ.ም. ተጽፎ ሥልጣን ማግኘቱን።

8. ብሉይ ኪዳንን ብቻ ያመለክት ነበር።

## ምዕራፍ አሥራ አምስት - መልሶች

1. በተጻፉበት ዘመን ቅደም ተከተል ሳይሆን እንደ ይዘታቸው መሠረት ነው የተወሰነው።

2. ሐዋርያት በሕይወት ስለነበሩና ለስብከትም እጅግ አስፈላጊ ስላልነበረ ነው።

3. ምክንያቱን አናውቅም።

4. በጣም መንግሥታዊ ስለሆነ ነው ይላሉ።

5. ጴጥሮስ ነበር።

6. የጴጥሮስ ጽሑፍ ነው ብለን እንገምታለን።

7. ማርቆስ ሳይሆን አይቀርም ዘገባውን ያጠናቀረው።

8. 606 ይገኛሉ።

9. 24 ይገኛሉ

10. 31 ብቻ ተጽፈው አይገኙም።

## ምዕራፍ አሥራ ስድስት - መልሶች

1. ማቴ.26-27፤ ማር.14-15፤ ሉቃስ 22-23 ናቸው።

2. የይሁዳ ሞትና የዘበኞች የኢየሱስን መቃብር መጠበቅ ጨምሮበታል።።

3. ምንም ሳያስቀር ነው።

4. የሽቶ መቀባትና የኢየሱስ የወታደሮቹ መዘባበቻ መሆንን አልተጠቀመበትም።

8. ማርቆስ ከጻፋቸው ነገሮች መካከል ምንም ለመተው አልፈለጉም።

9. በእርሱ ላይ የራሳቸውን በመጨመር ተጠቅመውበታል፤ ነገር ግን የጨመሩአቸው ነገሮች የተለያዩ ናቸው።

10. የጌቴሴማኒን ጸሎት ነው።

11. ሦስት ነጥቦች ጨምሯል፡- ኢየሱስ በቀያፋ ፊት መቆሙን፥ ጲላጦስ ሊፈታው ያደረገውን ሙከራና የኢየሱስ ጎን በጦር መወጋቱን።

## ምዕራፍ አሥራ ሰባት - መልሶች

1. በተአምራቱ ነበር።

2. የተለወጠውን የሰዎች ሕይወት ነው።

3. መንግሥቱ እንደ ደረሰ ማብሠሩ ነው።

4. የኢየሱስን መልእክት ግልጥልጥ ያደርጉታል።

5. ኢየሱስ ራሱ ስለ ራሱ የተናገረው ቃል ነው።

6. የክርስትና መሠረት ቢስ ሆኖ መገኘት ነው።

7. ዮሐ. 13-17 ነው።

## ምዕራፍ አሥራ ስምንት - መልሶች

1. በ5 ልንከፍለው እንችላለን።

2. 17 ድርጊቶች አዝሏል።

3. በ1፡1-39 ውስጥ ይገኛል።

4. ማቴ. 3-4ና ሉቃስ 3፡5-11 ናቸው።

5. 16 ናቸው።

6. ማር. 1፡16-20 ያለውን ነው።

7. ለማቴ. 5-7 ነው።

12. ማስተማርና ማሠልጠን የሚል ስም አለው።

13. በማቴ.8-12፡21 ነው።

14. የለምጻሙ መንጻት ታሪክና አምስት የተቃውሞ ታሪኮች ናቸው።

15. በማቴ. 9፡1-38፤ ማር. 2፡1-3፡6፤ ሉቃስ 5፡17-39።

16. ማቴ.5፡12 ማለት ክፍል 2ና 3 ናቸው።

17. የሚዳ ስብከት ብለነዋል።

18. በሉቃስ 6-7 ነው።

19. የአሥራ ሁለቱ ሥልጠና እንበለው።

20. በማቴ. 12-18፤ ማር. 3፡20-8፡38፤ ሉቃስ 8፡1-9፡50።

21. ሉቃስ ነው።

22. ማር.3፡13-19፤ ሉቃስ 5፡12-16።

## ምዕራፍ አሥራ ዘጠኝ - መልሶች

1. በማቴ. 24፡4-36 ነው።

2. በ8 ልንከፍለው እንችላለን።

3. የማቴ. 24፡26-28 ያለውን ነው።

4. በማር. 13 በቁ. 23 እና 24 መካከል መግባት ነበረበት።

5. ማቴ.24፡23-25 ስለ ሐሰተኛ መሢሐችና፤ ማቴ.24፡26-28 ስለ መብረቅ የተዘገበውን ትቷል።

6. በሉቃስ 24 በቁ.25 መካከል ነበር።

7. ለሠራተኞች የተሰጠ ማስጠንቀቂያ ነበር።

11. ስድስት ነገር ጨምሯል። ማቴ. 24፡37-25፡46

12. የሉቃስ የጉዞ ዘገባና ከኢየሱስ መያዝ በፊት የሆኑት ድርጊቶች ናቸው።

## ምዕራፍ ሃያ - መልሶች

1. የገሊላውን አገልግሎት ነው።

2. ውይይትና ንግግር በመሆኑ ነው።

3. ኢየሱስ ከአይሁዶች ጋር ብዙ ጊዜ ሲጋፈጥ ስለሚያሳዩ ነው።

4. ሀ. ኢየሱስ ቤተ መቅደስን ያፀዳው መቼ ነበረ?

   ለ. ኢየሱስ ከመያዙ በፊት ምን ድርጊት ተደረገ?

   ሐ. ኢየሱስ ለምን ያህል ጊዜ ሰበከ?

   መ. ፋሲካውን መቼ በላ? የሚሉት ናቸው።

5. ሳያውቃቸው አይቀርም።

6. ሐሙስ ሌሊት ሳይሆን አይቀርም።

## ምዕራፍ ሃያ አንድ - መልሶች

1. በ55 ዓ.ም. ገደማ ነበር።

2. ጳውሎስ አመንጪ ሳይሆን ተቀባይ መሆኑን ነው

3. ኢየሱስ ካስተማረው ጋር አይስማማም እያሉ ነው።

4. 3 እናገኛለን።

5. በሐዋ.2፡14-36፤ 10፡34-43፤ 13፡16-41 ነው።

6. ስምንት ይገኛሉ።

7. በጣም እንደሚመሳሰሉ እንመለከታለን።

4. 18ቱ ይገኛሉ።

5. በኢየሱስ ሥቃይ ላይ ነው።

6. በኢሳ.53 ላይ የሚገኙት መፈጸማቸውን ነው።

## ምዕራፍ ሃያ ሦስት - መልሶች

1. የብሉይ ኪዳን መክፈቻ ቁልፍ እንደሆነ አድርጎ ነው።

2. 8 ጊዜ ይገኛል።

3. የብሉይ ኪዳን ትንቢት የተፈጸመ መሆኑን ለማሳየት ነው።

4. በማቴዎስ 5-7፤ 10፤ 13፤ 18፤ 23-25።

5. ኢየሱስ ለሰበሰበው ኅብረተሰብ ነበር።

6. በ16፡18ና 18፡15-17 ነው።

7. አዲስ ማኅበር የተቋቋመ መሆኑን ለማሳየት አስቦ ነው።

8. በማቴዎስ 24፡3፤ 27፤ 37፤ 39 ውስጥ ነው።

9. የኢየሱስ ዳግም ምጽአት በአንድ መንገድ ከኢየሩሳሌም ውድቀት ጋር የተያያዘ መሆኑን ይጠቁማል።

10. የመከላከል፥ የማስተማርና የማጽናናት ዓላማ ነው።

## ምዕራፍ ሃያ አራት - መልሶች

1. ኅብረታቸውን አበላሽቷል።

2. ኢየሱስ ሲጠግነው ያመለክታል።

3. 2 ጊዜ ተጠቅሞበታል በሉቃስ 1፡47፥ 2፡11።

4. በተገለሉት፥ በሴቶችና በኃጢአተኞች ላይ።

1. ሎጎስና ሣርኤክስ ናቸው።

2. ኢየሱስ ስለ ራሱ የሰጠው ምስክርነት ነው።

3. ለኢየሩሳሌም አገልግሎት ነው።

4. ሁልጊዜ ተቃዋሚ መሆን ነው።

5. ከትምህርቱ ጋር በሚገባ በመዋሃድ ነው።

6. እግዚአብሔር የሚለግሠው ሕይወት ማለት ነው።

7. አሁን እንደ ተቋቋመች የሚያሳየውን ገጽታ ነው።

8. ወደፊት ስለመገለጡ በሚያመለክተው ገጽታ ነው።

## ምዕራፍ ሀያ ስድስት - መልሶች

1. ታቲያን ነበር።

2. በሶርያ ቋንቋ እና ለሶርያ ቤተ ክርስቲያኖች ነበር።

3. መሚሁ የመጣበትን ዓላማ የሚያበስር ማለት ነው።

4. እያንዳንዱ ልዩ ገጽታ ስለሚሰጠን ነው።

5. እንደ እነማቴዎስ ምሳሌዎች፥ በብዛት አይገኙበትም።

6. በእያንዳንዱ ወንጌል ብዛታቸውና ዓይነታቸው የተለያየ ነው።

7. ዮሐንስ ነው።

8. ማቴዎስ ነው።

9. ልዩ ዓላማ እንዳላቸው ያሳየናል።

## ምዕራፍ ሃያ ሰባት - መልሶች

1. የዮሐንስን ዓላማ ያሳየናል።

6. ኢየሱስን ከብሉይ ኪዳን መግለጽ ጋር በማዛመድ ነው።

7. የመጥምቁ ዮሐንስ አገልግሎትን ነው።

8. ስለ ገሊላና ይሁዳ አውራጃዎች ነው።

9. ዮሐንስ ነው።

10. የሚገኙትን ልዩነቶች ቅራኔዎች ናቸው ብለን እንዳንተች ነው።

11. ምንም አላደረጉም።

## ምዕራፍ ሃያ ስምንት - መልሶች

1. ጠቅላላውን አቀራረባቸው ልናስተውል ስንችል ነው።

2. በ11 ልንከፍላቸው እንችላለን።

3. ሀ. በመጥምቁ ዮሐንስ አገልግሎት።

   ለ. ወደ ኢየሩሳሌም በመግባቱ።

   ሐ. በሕማማቱ ዘገባ።

4. በትንሣኤው ላይ ነው።

## ምዕራፍ ሃያ ዘጠኝ - መልሶች።

1. በ51-52 ዓ.ም. ገደማ ጳውሎስ በቆሮንቶስ እንደነበረ ያሳየናል።

2. ከ33-52 ዓ.ም. ድረስ ነው።

3. በኢየሩሳሌም ነው።

4. ማንበብና መጻፍ ይችሉ ነበር።

5. ሐዋርያት ነበሩ።

6. ከ40-66 ዓ.ም. ነው።

10. ሁሉም የተጻፉት ከ70 ዓ.ም. በፊት ነው።

## ምዕራፍ ሠላሳ - መልሶች

1. ኢየሱስ የመጣበትን ምክንያት ማብራራት ነበረ።

2. ወንጌሉ አንድ ብቻ መሆኑን ያሳየናል።

3. የአንዱ ወንጌል አራት ገጽታዎች ናቸው ለማለት እንችላለን።

4. ሀ. ከብሉይ ኪዳን ጋር ስለተያያዙ ነው፥

ለ ኢየሱስ ስለተረጎማቸውና

ሐ. ሕይወትን የመለወጥ ኃይል ስላላቸው ነው።

5. ኢየሱስ ራሱ ነበር።

6. ድርጊቶችን ከመዘርዘራቸው በላይ ለእነርሱ ደግሞ ትርጉም ስለሰጡ ነው።

## ምዕራፍ ሠላሳ አንድ - መልሶች

1. ከኃጢአት ኃይል ነጻ መውጣት ማለት ነው።

2. ኢየሱስ ራሱ ነው።

3. ወንጌል ሲሰበክ ነው።

4. የዓይን ምስክሮች ነበሩ።

5. የመንፈስ ቅዱስ ምሪትን ነው።

6. ስሕተት መፈጠር ነው።

7. ምንም ስሕተት የላቸውም ማለት እንችላለን።

8. የወንጌላውያኑ ዘገባ ነው።

= = = = = = = = = = = = = = // = = = = = = = = = = = = = =